- በእግዚአብሔር ማመኑ በአቀረበው ከበጎቹ መንጋ በመጀመሪያ በተወለደው የአንድ ጥቦት መስዋዕት ተገልጦ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት በዕብራዊያን መጽሐፍ ምዕራፍ አሥራ አንድ ላይ የተጠቀሰው የመጀመሪያ ሰው አቤል የአዳም ልጅ ነው። ዘፍ 4:4

- በዕብራዊያን ምዕራፍ አሥራ አንድ ላይ የተጠቀሱትን የእግዚአብሔር ሰዎች በሙሉ ብንመለከት በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ምንም ስህተት ያልፈጸሙ ሳይሆኑ በእምነታቸው እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘታቸው የተመሰከረላቸው በሕሊናና በሙሴ ሕግ ዘመን የኖሩ ሰዎች ናቸው።

- እምነት ከዘላለም የነበረና ለዘላለም የሚኖር ነው።

- ጻድቅ በእምነቱ የዘላለም ሕይወትን ያገኛል።

- በአሮጌውም ይሁን በኢዲስ ኪዳን ጻድቃን የሆኑ ሁሉ ኃጢአተኞች የነበሩና በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነት ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረላቸው ናቸው።

- እምነቱ "ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት" የሚለው ቃል የተጻፈው ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን ለእኛም፣ እምነታችን ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርልናል።

- በአዲስ ኪዳን ማንም በአንዱ አምላክ በእግዚአብሔር የሚያምን ሁሉ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ እንዲቆጠርለት አንድ የእምነት ሥራ በእርሱ መገለጥ አለበት፣ ይህም አንዱና ብቸኛው የእምነት ሥራ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እርሱ ኃጢአት እንደተሰቀለና እርሱን ለማጽደቅ ከሞት መነሣቱን ማመን ነው።

- ክርስቶስ ወደ እርሱ ለሚመጡ ከዘላለም ጥፋት የሚሰውር የደኅንነት መርከብ ከሰይጣን ጨለማም የሚያወጣ የደኅንነት ብርሃን ነው።

ክፍል ዘጠኝ

አርእስትህን መምረጥ

"፤ኑሮዬ ይበቃኛል ስሚሰው ግን **ስግዚአብሔርን ማምለክ** እድግ ማትረፊያ ነው።" 1ጢሞ 6:6

ምዕራፍ ስድስት

ክርስቶስን መምሰል

"ፈጥኜ ወደ አንተ እንድመጣ ተስፋ አድርጌ ይህን እጽፍልሃለሁ። ብዘገይ ግን በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው። እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤

በሥጋ የተገለጠ፤

በመንፈስ የጸደቀ፤

ለመላእክት የታየ፤

በአሕዛብ የተሰበከ፤

በዓለም የታመነ፤

በክብር ያረገ።" 1ጢሞ 3:14-16

በሥጋ የተገለጠ፤ በመንፈስ የጸደቀ፤ ለመላእክት የታየ፤ በአሕዛብ የተሰበከ፤ በዓለም የታመነ፤ በክብር ያረገ ማነው? ጌታ ኢየሱስ አይደለምን? እግዚአብሔርን መምሰልን በምድር ላይ እንደ ኢየሱስ በሙላት የገለጠ ማንም የለም። እግዚአብሔርን ስለ መምሰል ስንናገር የምንናገረው ክርስቶስን ስለ መምሰል ነው።

ጳውሎስ "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።" ብሎ በ1ቆሮ 11:1 ላይ ሲናገር ምን ማለቱ ነው? ለመሆኑ እርሱ ክርስቶስን በምንድን ነበር የመሰለው? በአምላክነቱ በጌትነቱ በመድኃኒትነቱ ነበርን? አልነበረም። ጳውሎስ ክርስቶስን የመሰለው በባህሪው ፍለጋውንና ምላሌውን በመከተል ነበር። ምላሌውም ለእግዚአብሔር ፈቃድ መሰጠትና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ነበር። 1ጴጥ 2:21 ጳውሎስ እኔን ምሰሉ ሲል እንደ እርሱ

ለሐዋርያነት አገልግሎት ሁሉም መሰማራት እንዳለበት ለመግለጽ ነውን? በፍጹም አይደለም። ይልቅ እርሱ ክርስቶስን በባህሪው እንደ መሰለውና ፍለጋውን እንደተከተለ እነርሱም በዚህ አቅጣጫ ጳውሎስን በመምሰል በተዘዋዋሪ ኢየሱስን እንዲመስሉ እንጂ።

1ጢሞ 6፡10-11 አማኞች ገንዘብ መውደድን እንዲሸሹ ካሳሰበ በኋላ ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርን፣ መጽናትን፣ የዋህነትን እግዚአብሔርን ከመምሰል ጋር መከታተል እንዳለባቸው ያዛል።

እግዚአብሔርን መምሰል ሲፈልግ ሰይጣን ለምንድን ነበር በሰማይ ካለው ስፍራ የተጣለው? ኢሳ 14፡12-16፣ ሕዝ 8፡19 የአሁኑ ሰይጣን የቀድሞ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ እግዚአብሔርን መምሰል የፈለገው በባህሪው ሳይሆን በአምላክነቱ ነበር። በልቡ በመታበይ እንደ እግዚአብሔር መመለክ በመፈለጉ ነበር።

"አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፣ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! . . . አንተም በልብህ፣ ወደ ሰማይ አርጋለሁ፣ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፣ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፣ ከደመናዎች ከፍታ በላይ አርጋለሁ፣ **ዘወውልም** **እመሰላለሁ** አልህ። ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጉድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ።" ኢሳ 14፡12-15

በዘፍ 3፡22 ላይ እግዚአብሔር አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ ያለው በምንድን ነበር? የሰማይና የምድር አምላክ የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ በመሆን ነበር? አልነበረም፣ እግዚአብሔር አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ ያለው መልካምንና ክፉውን በማወቅ ነበር። በዘፍ3፡5 ላይም ሰይጣን ይህንኑ ለሄዋን ነግሮአታል። ከአብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ውጪ የሰማይና የምድር አምላክ ፈጣሪ በሰማይም በምድርም ማንም የለም፣ ወደፊትም ሊሆን የሚችል የለም።

አዳም ማወቅና መከተል የነበረበት እግዚአብሔርን ብቻ ነበር። ሰው ክፉውን ወይም ሰይጣንን ማወቅ አያስፈልገውም ነበር። ሰይጣን ሄዋንን ክፉውን ማወቅ ሞትን የሚያመጣ ነገር ሳይሆን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚያስጥል ያህል ተፈላጊ ነገር እንደሆነ እንድታይ ነበር ያደረጋት። ነገር ግን ክፉውን ማወቅና ማድረግ ሞትን ወደ ሰው ልጅ አምጥቷል። እግዚአብሔርንና ጌታ ኢየሱስን ማወቅ ደግሞ የዘላለም ሕይወት ነው። ዮሐ 17፡3 እግዚአብሔር እርሱን እንደ ማወቅና እንደ ምሕረት ከሰው የሚፈልገው ሌላ ነገር የለም።

"ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፣ ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ **እግዚአብሔርን** **ማወቅ** እወድዳለሁና። እነርሱ ግን **እንደ** **አዳም** ቃል ኪዳኔን ተላልፈዋል፣ በዚያም ላይ ወንጅለውኛል።" ሆሴ 6፡6-7

አማኝ ክርስቶስን በባህሪው እንዲመስል ተጠርቷል። ለዚህም በዳግም መወለድ አዲስ ሰው በውስጡ ተፈጥሯል። ኤፌ 4፡20-24

"የመለኮቱ ኃይል፣ በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፣ ስሕይወትና **እግዚአብሔርን** **ለመምሰል** የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን፣ በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት ስለምትችሉ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፣ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን።" 1ጴጥ 1፡2-5

አማኝ እግዚአብሔርን ለመምሰል የተጠራው ገንዘብ እንዲለበስብበት ተብሎ አይደለም። 1ጢሞ 6፡4-5 ሰው ለመኖርና የጌታን ጥሪ በሕይወቱ የሚያሳካበት ያህል ገንዘብ ካለው ይበቃዋል። ከገንዘብ በላይ የሚያስፈልገውና አማኝ ዓላማዬ ብሎ ለመሰብሰብ ሊተጋበት የሚገባው ነገር እግዚአብሔርን መምሰል ነው። 2ጴጥ 1፡7 በግልጽ እንደሚያሳየው ክርስቶስን መምሰል እየበዛና እየጨመረ

ሊመጣ የሚችል ነገር ነውና። ገንዘብ ለብዙ ነገር ይጠቅማል እግዚአብሔርን መምሰል ግን 1ጢሞ 4:8 እንደሚናገረው የአሁንና የሚመጣው ዓለም ተስፋ ስላለው ለነገር ሁሉ ይጠቅማል።

"፤ኑሮዉ ይበቃኛል ለሚለው ግን **እግዚአብሔርን መምሰል** እድግ ማትረፊያ ነው።" 1ጢሞ 6:6

ጳውሎስ በ1ጢሞ 6:7-8 ምግብና ልብስ ከኖረን ይበቃናል ሲል መቼም ለመኖርና የጌታን ጥሪ ለማሳካት የሚያስችል መሠረታዊ ፍላጎታችን ከተሟላልን ለማለት እንጂ ከምግብና ከልብስ ውጪ ምንም ነገር ለምሳሌ፣ ቤት እንኳ አያስፈልገንም ለማለት ሊሆን አይችልም። የጳውሎስን ሕይወትና አገልግሎት ያጠና ጎዳና ተዳዳሪ የሚሆኑ አማኞችን የማፍራት ፍላጎት ሊኖረው እንደማይችል በቀላሉ ሊረዳው የሚችል ጉዳይ ነው። ሆኖም ግን አማኝ በምድር ላይ የተጠራበትን ጥሪ ለማሳካትና እንደ ተጠራበት ጥሪ ያህል ለመኖር የሚያስችል ገንዘብ ካለው ይበቃዋል። ለዚህም ሆነ ለሌላ ለማንኛውም ነገር ደግሞ እግዚአብሔርን መምሰል ይጠቅማል።

እግዚአብሔርን እንድንመስለው የሚያደርጉ ባህሪያት ደግሞ በመንፈስ ፍሬ ውስጥ በስፋት ተገልጸዋል። በሌላው አነጋገር የሥጋ ሥራን በማስወገድ የመንፈስ ፍሬን የሚያፈራ አማኝ እግዚአብሔርን እየመሰለ ይመጣል። ስለሆነም ከዚህ በመቀጠል የመንፈስ ፍሬን ምንነት በስፋት የምናይ ሲሆን በቀጣይ ምዕራፎች ደግሞ የሥጋ ሥራን ስለማስወገድና የመንፈስ ፍሬን ስለማፍራት በሌላ አነጋገር እግዚአብሔርን በመምሰል እየጨመሩ ስለ መምጣት እንመለከታለን። የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። ገላ 5:22

1. ፍቅር

እግዚአብሔር በባህሪው ፍቅር ነው። ፍቅር መሠረታዊ የሆነ የእግዚአብሔር ባህሪ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር (በግሪኩ "አጋፔ") ሰው ለወላጆቹ፣ ለጓደኞቹ፣ ለሀገሩ፣ ወ.ዘ.ተ ካለው ፍቅር የተፈጥሮ ፍቅር (በግሪኩ "ፊሊያ") እንዲሁም በተቃራኒ ፆታዎች መካከል ካለው በተለምዶ እውር ነው ከሚባለው ፍቅር (በግሪኩ "ኤሮስ") እንዲሁም ለይጣን በውሸት ለሰዎች አለኝ ከሚለው ሕይወትን ከመስጠት ይልቅ ሰዎችን በመግደል ከሚገለጠው አጋንንታዊ ፍቅር ፈጽሞ የተለየ ነው።

ከፈሪሳውያን ከሰዱቃውያን መካከል አንድ ሕግ አዋቂ ጌታ ኢየሱስን ሊፈትነው፣ መምህር ሆይ ከሕግ ማናችይቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት? ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ወደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፦ እርስዋም፦ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። ካለው በኋላ ሌላ ተጨማሪ መረዳት ሲጨምርለት፣ በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል አለው። ማቴ 22:35-40

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም፦ ፍቅር ለእግዚአብሔር ሲደመር ፍቅር ለባልንጀራ እንዴት ፍቅር ለባልንጀራ ይሆናል? የዚህን ስሌት ምሥጢር ሐዋርያው ዮሐንስ በመጀመሪያው መልእክቱ ምዕራፍ 4 ቁጥር 20-21 ላይ ገልጾታል። በዚህም ክፍል እንደምንመለከተው ማንም፦ እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፣ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔር ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእግዚአብሔር አለችን። ባልንጀራውን የሚወድ እግዚአብሔርን እንደሚወድ ያሳያል። አስተውል፦

በእግዚአብሔር ፍቅር መኖራችን የሚፈተነው እግዚአብሔርን እንወደዋለን ብለን በመናገራችን ሳይሆን ባልንጀራችንን በመውደዳችን ነው።

እግዚአብሔርን የሚወድ እርሱን ደስ ለማሰኘት ቃሉን ይጠብቃል። የእግዚአብሔርም ትዕዛዝ፦ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ ትእዛዙንም እንደሰጠን እርስ በእርሳችን እንዋደድ ዘንድ ነው። 1 ዮሐ 3:23

"ስብ እንደወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ በፍቅሬ ኑሩ። እኔ የአባቴን ትዕዛዝ እንደጠበቅሁ በፍቅረም እንደምናር ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትናራላችሁ"

ዮሐ 15:9-10

በተጨማሪ 1 ዮሐ 3:11-24፣ 1 ዮሐ 5:6፣ ዮሐ 14:15 ተመልከት። ከላይ ያለውን ሀሳብ ስናጠቃልለው ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማል፤ ይኸውም፣ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚል ነው። ይህን ትዕዛዝ በጥልቀትና በስፋት ስናጠና የሚከተለውን መረዳቶች እናገኛለን።

ባልንጀራን እንደ እራስ አለመውደድ እንጂ እራስን መውደድ ኃጢአት አይደለም። እራስ ወዳድ የሚባል ሰው እራሱን የሚወድ ሳይሆን ባልንጀራውን እንደ እራሱ የማይወድ ወይም ከባልንጀራው በላይ እጅግ እራሱን የሚወድ ነው።

ባልንጀራን እንደ እራስ አለመውደድ ብቻ ሳይሆን እራስን መጥላትም ኃጢአት ነው። በአንድ ጎብረተሰብ እጅግ የከፋ የአጥፍተህ ጥፋ ወንጀል ውስጥ የሚሰማሩ እራስ ወዳድ ከሆኑ ሰዎች ይልቅ እራሳቸውን የሚጠሉ ሰዎች ናቸው። እነዚህ እራሳቸውን የሚጠሉና የሚያንቋሸሹ ሰዎች ሌሎችን ሰዎች ለማክበር እጅግ ይቸገራሉ።

እራስን መጥላት፣ ማንቋሸሽ፣ መስደብ፣ ወ.ዘ.ተ ጽድቅን ማድረግና እግዚአብሔርን የሚያስደስት ስለሚመስላቸው በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት እራሳቸውን የሚሳደቡ ቅዱሳን ጥቂት አይደሉም። በአብዛኛው እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ እራስን መካድ፣ ለእግዚአብሔር እራስን ማዋረድና መስቀልን መሸከም፣ እራስን ለክርስቶስ ባዶ ማድረግ፣ ወ.ዘ.ተ የሚሉ አባባሎች ትርጉም የተዛነፈባቸው ናቸው። እነዚህ አባባሎች በምንም መልኩ ቢወሰዱ ክርስቲያን እራሱን እንዲሰድብና እንዲጠላ የሚናገሩ አይደሉም። አባባሎች ከአውደ ንባባቸው ውጪ ከተተረጐሙ የተዛባ ትርጉም ሊሰጡ ስለሚችሉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። እስቲ ለመረዳት ጥንቃቄ ከሚጠይቁ ክፍሎች ለምሳሌ በሉቃ 14:26-27 ያለውን እንመልከት።

"ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የእራሱን ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ፤ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም። ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ፤ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።"

ለመሆኑ በዚህ ክፍል ጌታ ኢየሱስ የእርሱ ደቀ መዝሙር ለመሆን ባልንጀሮቻችንንና እራሳችንን መጥላት እንዳለብን ይሆን የሚናገረው? በፍጹም አይደለም። እንደዚያማ ከሆነ ስለምን "እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትዕዛዝ አሰጣችኋለሁ። እርስ በእርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፤ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።" አለ? ዮሐ 13:34-35

ሉቃስ 14:24-26 የሚያስተላልፈው መልእክት ታዲያ ምንድንነው? የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ለመሆን የሚፈልግ ስለ ክርስቶስ መከራን ሁሉ መታገሥ አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የእራሱን

ሕይወት እንኳ ለመክፈል፣ ለእግዚአብሔር ፍቃድ አሳልፎ ለመስጠት የተዘጋጀ መሆን እንዳለበት የሚገልጽ ነው።

ለማንኛውም የአዲስ ኪዳን ትእዛዝ ባልንጀራህን እንደ እራስህ ውደድ የሚል ነው። ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይህን ብቸኛ እና ሕግ ሁሉ የተፈጸመበትን ትእዛዝ ሳይቃረን መተርጉም አለበት። ይህን ትዕዛዝ ከአንድ ግለሰብ (ባልንጀራ) እይታ ውጪ እንደዚህ ልናሰፋው እንችላለን።

ባልንጀራህን እንደ እራስህ ውደድ፣
ሌሎችን ቤተሰቦች እንደ ቤተሰቦችህ ውደድ፣
ሌሎችን ብሔረሰቦች እንደ ብሔረሰብህ ውደድ፣
ሌሎችን ሀገሮች እንደ ሀገርህ ውደድ፣
ሌሎችን አጥቢያ በተክርስቲያኖች እንደ አጥቢያ ቤተክርስቲያንህ ውደድ፣

ይህ ትዕዛዝ በተገላቢጦሹም ይሠራል።

እራስህን እንደ ባልንጀራህ ውደድ፣
ቤተሰብህን እንደ ሌሎች ቤተሰቦች ወደድ፣
ብሔረሰብህን እንደ ሌሎች ብሔረሰቦች ውደድ፣
ሀገርህን እንደ ሌሎች ሀገሮች ውደድ፣
አጥቢያ ቤተክርስቲያንህን እንደ ሌሎች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውደድ፣

ክርስቲያን የሁለት ሀገር መንግሥት የእግዚአብሔር መንግሥትና በምድር ላይ ያለው የሀገሩ መንግሥት ዜጋ መሆኑን እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ በማቴ 5:43 ያለውን ማስተዋል ከላይ ያሉትን ትዕዛዛት ለማጣጣም ይረዳዋል።

"ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረገሙአችሁንም መርቁ፦ ስሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፦ ስለሚያሳድዱአችሁ ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፤ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናብን ያዘንባልና። የሚወዷችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።"

ክርስቲያን በፍጹም ጥላቻ ሊጠላ የተገባው ሰይጣንና መላእክቱን እንዲሁም ማንኛውም ዓይነት የጨለማ ሥራን ነው። አንድ ሰው ክርስቲያን እንደሆነ ብዙም ሳይቆይ የሚረዳው ነገር ቢኖር እግዚአብሔርን እየወደደ የመጣውን ያህል ሰይጣንን እየጠላ መምጣቱን ነው። ማንም ኃጢአትን የሚጸየፈው ጽድቅን የወደደውን ያህል ነው። እግዚአብሔርንና ሰይጣንን አንድ ላይ መውደድ አይቻልም። ያዕ 4:4

ይህን ሁሉ እያነበብን እያለ አንድ አብይ ጥያቄ በአእምሮአችን ሊመላለስ ይችላል። ይኸውም፦ ፍቅር ማለት እራሱ ምንድን ነው? በተለይ በዚህ ክፍል እየተመለከትን ያለነው በግሪክ ቋንቋ አጋፔ የተባለው መለኮታዊ ፍቅር ምንድን ነው? ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆንን ብርሃን 1 ዮሐ 4:7-21 ይፈነጥቅልናል። ቁጥር 10 እንዲህ ይላል፦

"ፍቅርም እንደዚህ ነው እግዚአብሔር እርሱ አራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም"

እግዚአብሔር ፍቅር ነው የተባለው ሰዎች ሁሉ ስለወደዱት ሳይሆን እርሱ ሰዎችን ሁሉ ስለወደደ ነው። ከዚህም ፍቅር ማለት መውደድ መሆኑን ልንረዳ እንችላለን። ፍቅር መውደድ እንጂ በጭራሽ መወደድ አይደለም። ፍቅር መወደድ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ፍቅር ነው ማለት ባልተቻለም ነበር፤ እግዚአብሔርን ሁሉም ሰው አይወደውምና!

ለመሆኑ እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ እንደሚወድ በምንድነው የተገለጠው? ለሰዎች ኃጢአት ማስተሰሪያ የሚሆን አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሰማይ ወደ ምድር በመላኩ አይደለም? ከዚህም መውደድ በመስጠት እንደሚገለጥ እናያለን። ፍቅር መውደድ ሲሆን መውደድም መስጠት ነው። በተዘዋዋሪ ፍቅር መስጠት ነው። ከብርና ከወርቅ አልፎ እራስን ለወዳጆቹም ጠላቶቹ ለሆኑም ሰዎች አሳልፎ የሚሰጥ መለኮታው ፍቅር ነው። ሮሜ 5:6-11። የሚሰጥ የሚመስል ሁሉ የሚወድ ባይሆንም የሚወድ ሁሉ ግን ይሰጣል፤ ያለውን፣ እራሱን ለመስጠት የተዘጋጀ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ 15:12-13 ባለው ክፍል እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በእርሳችሁ ትወደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት ካለ በኋላ ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ሰማንም የሰውም ብሏል። ማንም ሊወድህ የሚችለው እራሱን አስኪሰጥህ ድረስ ብቻ ነው። የጌታን ፍቅር የተረዳነው ገና ኃጢአተኞችና የጌታ ጠላቶች ሳለን ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ስርየት ለእኛ በመሰጠቱ ነው። ጌታ ሰዎችን የወደደው ለእነርሱ እንደ እነ አብርሃም፣ ሙሴ፣ ኤልያስ፣ ጳውሎስ፣ ጴጥሮስ፣ ወ.ዘ.ተ ያሉ ነቢያትንና ሐዋርያትን አስኪያስነሳላቸው፤ እንደ እነ ገብርኤል፣ ሚካኤል ያሉ መላእክቶችን አስኪልክላቸው ድረስ ብቻ አይደለም፤ በሰማይ፣ በምድር፣ ከምድር በታች የጌቶች ጌታ የሆነውን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለ ኃጢአታቸው ስርየት ለመስቀል ሞት አሳልፎ እስከ መስጠት እንጂ!

የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፡- እግዚአብሔር በሰማይም ይሁን በምድር ማንም ሊወደድበት በሚችልበት በመጨረሻውና በከፍተኛው ፍቅር ይወድሃል። በቅዱሳን ሰዎችም ይሁን በቅዱሳን መላእክት መቅናት አያስፈልግህም፤ እግዚአብሔር ከአንተ እኩል እንጂ ከአንተ በላይ የሚወደው የለምና! ለዚህ ነው በበደልህ ሙት በሆንህ ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት በመስጠት ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ያስቀመጠህ። ኤፌ 2:4-7

ልብ በል፡- እግዚአብሔር ለሰዎች ያለው ፍቅር የተመዘነው በየትኛውም ቅዱስ መልአክ ወይም ጻድቅ ሰው ሳይሆን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለዚህ ነው 1 ዮሐ 3:16 እርሱ (ኢየሱስ) ስለ እኛ ነፍሱን ስላኖረ ስጥችስለና በዚህ ፍቅርን ስውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን ስላልፈን እንድንሰጥ ይገባናል የሚለው። 1 ዮሐ 4:9-12

ፍቅር ከስሜት የሚመነጭ ነገር ሳይሆን ከመንፈስ ቅዱስ የምንቀበለው ነው። ስሜታችን አንድን ሰው ሲጠላው ለስሜታችን ከመገዛት ይልቅ ስሜታችንን ገዝተን ያንን ሰው እንደምንወደው ልንነግረውና በተግባርም ልንገልጽለት እንችላለን። በፍቅር የምትመላለሰው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመተባበር በፍቅር ለመመላለስ በመምረጥና በመወሰን እንጂ የስሜት ሕዋሳትህን እያደመጥህ አይደለም። ሁልጊዜ ስሜቱን የሚታዘዝ በስሜት ይመላለሳል እንጂ በመንፈስ አይመላለስም። ስሜቱን በመንፈስ ቅዱስ የሚገራ ግን የመንፈስ ደስታ ደስታው እየሆነ ይመጣል።

በእግዚአብሔር ፍቅር ዕለት ዕለት የሚሞላ ሰው ነው ባልንጀራውን እንደ እራሱ የሚወደው። በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጣቸው በመንፈስ ቅድስ አማካኝነት ያለ በመሆኑ ከእነርሱ የሚጠበቀው በእግዚአብሔር ፊት በመቅረብ ዕለት ዕለት በዚህ ፍቅር መሞላት ነው።

እግዚአብሔር ወደ እርሱ የሚቀርቡትን የፍቅር ጥማት ያረካል። ክርስቲያንም ሁልጊዜ የፍቅር ጥማቱ እንዲረካ የፍቅር ምንጭ ከሆነው አምላኩ ጋር ሁልጊዜ ጎብረት ሊያደርግ ይገባዋል። በተጨማሪ የእግዚአብሔር ቃል ስለ ፍቅር የሚናገረውን በማጥናት ፍቅሩ በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ መትጋት አለበት። ፊል 1:9-11፣ 2 ጴጥ 1:5-7

"የእግዚአብሔር ፍቅር በሰማይና በምድር ያሉ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ፤. . . ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ስማስተዋል ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ስማወቅ ትበረቱ ዘንድ፣ እስከ እግዚአብሔርም ፍፁም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ።" ኤፌ 3:14-19

ፍቅር መስጠት መሆኑን አሁን የተረዱ አንዳንዶች አንድ ጥያቄ ወደ እነርሱ ሊመጣ ይችላል። ፍቅር መስጠት እንዴት ይሆናል? ሰይጣንስ አንዳንድ መልካም ነገሮችን ይሰጥ የለም? በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስን ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ በጥንቃቄ ያነበበ አንድም ጊዜ የሰይጣን ቸርነትና ሰጪነት እንዳልተገለጠ ያስተውላል። ጌታ ኢየሱስ ስለ ሰይጣን በዮሐ 10:10 ላይ ሲናገር ሰይጣንን ሌባው ይለውና ሌባው ሊሰርቅ፣ ሊያርድ፣ ሊያጠፋ እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም ብሏል። ቸር ወይም ሰጪ እግዚአብሔር ነው።

ሰይጣንን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያውቀው በሌባነቱ፣ በአታላይነቱ፣ በውሸታምነቱ፣ በሽንጋይነቱ፣ በገዳይነቱ፣ በአጥፊነቱ፣ ወ.ዘ.ተ ነው። ሰይጣን ለሰዎች አንዳንድ መልካም የሚመስሉ ስጦታዎች ሰጥቶ ከእግዚአብሔር በመለየት የሰጠውን ስጦታም ጭምር መውሰዱ አታላይ እንጂ እንዴት ሰጪ ያሰኘዋል? ያዕ 1:16-17 እንዲህ ይላል፣

"የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ አትሳቱ በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፣ መሰወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ

ከሌለ ክብርሃናት አባት ይወርዳሉ። ስፍጥረቱ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል ስስቦ ወስደን።"

ከዚህ በኋላ በአካባቢህ በምታየው ነገር ሳትታለል መጽሐፍ ቅዱስ የሰጠውን እውቅና ለሰይጣን ሰጠው፣ ሰይጣን ሌባ እንጂ ሰጪ አይደለም። ሆኖም ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰይጣንም ይሁን ማንም ኮፒ ሊያደርገው በማይችል ሁኔታ ነው ፍቅሩን ለሰው ልጆች የገለጸው፣ እራሱን ለመስቀል ሞት ስለ እነርሱ አሳልፎ በመስጠት። ስመሆኑ በምድር ላይ በሺ የሚቆጠር ሃይማኖትና የሃይማኖት መሪዎች እንዳሉ ሰምተህ ከሆነ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን ጠላቶቹ ለሆኑ ሰዎች አሳልፎ የሰጠ የሃይማኖት መሪ ሰምተሃል? በጭራሽ የለም። የክርስቶስ ፍቅር ስኖ በክርስቶስ ፍቅር የተመሠረተው ክርስትና ከሁሉም ቧዩ የሚያደርገው ስንዴና ዋናው በቀሬንዮ መስቀል መጻፉቹ ብቻ ሳይሆን መሳቶቹ ሰሆኑ ሰሰው ልጆች ሁሉ ደኅንነት የተገሰጠው የክርስቶስ ፍቅር ነው።

ሰይጣን ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ነገሮችን ኮፒ ቢያደርግም የክርስቶስን የመስቀል ላይ ፍቅር ግን ኮፒ ማድረግ አልቻለም። ብዙ የተለያዩ ሃይማኖቶች በመጻሕፍቶቻቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ነገር ኮፒ ቢያደርጉም የክርስቶስን የመስቀል ላይ ፍቅር ግን ኮፒ ማድረግ አልቻሉም። የመስቀሉ ቃል ለእነርሱ ሞኝነት ሲሆንባቸው በስብከት ሞኝነት ለሚያምኑት ግን የሚያድን የእግዚአብሔር ኃይል ነው። 1 ቆሮ 1:18-21

አንድ የእግዚአብሔር ጠላት የነበረ ኃጢአተኛ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ሲቀበል እግዚአብሔርን መውደድ ይጀምራል። ለዚህ ነው 1 ዮሐ 4:19 ላይ ዮሐንስ እርሱ (እግዚአብሔር) አስቀድሞ ወዶናልና አሁን እኛ እንወደዋለን ያለው።1 ዮሐ 4:15-19 የእግዚአብሔር ፍቅር ለሰዎች በሰዎቹ ማንነት ላይ የተደገፈ አይደለም። ይህ ቢሆን ኖሮ ሰዎች ተወዳጅ

ሊያደርጋቸው የሚችለው ባህሪያቸው ከአዳም ውድቀት በኋላ የተበላሸ በመሆኑ ከዚያ በኋላ የሚወደድ ነገር ስለሌላቸው የጌታን ፍቅር አያገኙም ነበር።

በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ በዓለም የሚኖሩ ሰዎችን ሁሉ እንዲሁ ያለ ምንም ምክንያት ወዷልና እኛም ሰዎችን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ወይም ምክንያት እንድንወድ ታዘናል። ይህም ለሰዎች ሁሉ በጎ በማሰብ፣ በጎ ቃል በመናገር፣ በጎና መልካም ሥራዎችን ወይም ስጦታዎችን እራስን እስከ መስጠት በመስጠት የሚገለጽ ነው። ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፣ ወንድሙም የሚያስፈልገው ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን፣ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? ወገኖች ሆይ፣ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ አንዋደድ 1 ዮሐ 3፡17-18። እርግጥ በሥራ ቀርቶ በአንደበት መልካም ቃል እንኳ በተለይ ምክንያት ደርድረው ለሚጠሉአቸው ሰዎች መናገር ጭንቅ የሚሆንባቸው ይልቁን የሚራገሙ፣ ሰዎችን ለመግደል የሚሯሯጡ ወ.ዘ.ተ አይኖሩም ይሆን? አንተ ግን ለባልንጀራህ ያለህን ፍቅር በአንደበትህ በሥራም ለመግለጥ ልትተጋ ይገባሃል።

ከዚህ በኋላ ፍቅር መውደድ መሆኑ የገባው ለመወደድ ማገልገልና መሯሯጥ ያቆማል። ከሚወዳቸውም ሰዎች ሁሉ የፍቅር ምላሽ አይጠብቅም። ክቤተሰቡ፣ ከጓደኞቹ፣ ከሥራ ባልደረቦቹ፣ ከጐረቤቱ፣ ወ.ዘ.ተ የሚጠላው ሰው ሲያጋጥመው፣ ተጠላሁኝ፣ እንዴት ተጠላሁ እያለ ከመበሳጨትና ከማዘን ይቆጠባል፣ ፍጹም የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንኳ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ይጠሉት የነበሩ ሰዎች እንደነበሩ በማሰብ ክፉውን በመልካም ለማሸነፍ ይተጋል። አንዳንድ ጊዜ እስከ መጨረሻው ብንወዳቸውም ከጠላትነታቸው የማይመለሱ ሳዖል ለዳዊት የዕድሜ ልክ ጠላት እንደሆነ እስከ መጨረሻው እኛን በመጥላት የሚዘልቁ ሰዎች በሚያጋጥሙን ጊዜ ግር ልንሰኝ አይገባም። 1 ሳሙ 18፡29

እዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፍ ነገር ቢኖር በሰውና በመላእክት ፍጥረታት ሁሉ የሚወደድ ማንም የሌለ መሆኑን ነው። እግዚአብሔርንም እንኳ አስቀድሞ እንዳየነው የሚጠሉት አሉ። ቢያንስ ሰይጣን እንኳ ምን ያህል ሊጠላው እንደሚችል ማየት ይቻላል። አንዳንድ ክርስቲያኖች ልዩ የፍቅር ሰው ብሆን ሰው ሁሉ ይወደኝ ነበር ብለው ያስባሉ። ሆኖም ግን ምንም ዓይነት የፍቅር ሰው ቢሆኑ ሰው ሁሉ አይወዳቸውም። እግዚአብሔርም በሰዎች ሁሉ እንዲወደዱ አላዘዛቸውም፣ ሰዎችን ሁሉ እንዲወዱ እንጂ።

ሰዎች ሁሉ እንዲወዱን ማድረግ ባንችልም፣ ሰዎችን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ በመኖር መውደድ ይቻላል። ስለሆነም የጌታን ፍቅር ለሰው ሁሉ በመስጠት እና ፍቅር ሊሰጡን ከሚፈቅዱ እየተቀበልን እንመላለስ። እግዚአብሔር ፍቅር እንደ መሆኑ የእግዚአብሔር መንፈስ የፍቅር መንፈስ ነው፣ የእግዚአብሔር መንግሥትም የፍቅር መንግሥት ነው። ሮሜ 5፡5፣ ቆላ 13፡14

ፍቅር በዚህ ዓለም እና በሚመጣው ያለና የሚኖር እንዲሁም እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠው ትልቅ ስጦታ ነው። 1 ቆሮ 13፡13። 1 ቆሮ 12፡31 የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ ካለ በኋላ የጸጋ ስጦታን ጨምሮ ፍቅርን ከሁሉ የሚበልጥ መንገድ ይለዋል። ይህንንም 1 ቆሮ 13፡1-3 ይበልጥ ሲያብራራው እንዲህ ይላል፦

"በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር . . . ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።"

ስለሆነም የጸጋ ስጦታን በብርቱ እንፈልግ ፍቅርን መከታተል አለብን። 1ቆሮ 14፡1 የክርስቲያን ሕይወቱና አገልግሎቱ በሙሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተመሰገነ እንዲሆን በፍቅር መቃኘት አለበት። በመላእክትና በሰዎች ልሳን ሲናገር በፍቅር፣ ትንቢት ሲናገር በፍቅር፣ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትንም

ሁሉ ሊያውቅ በፍቅር፣ ድሆችን ሊመግብ በፍቅር ሥጋውን በአሳት አሳልፎ ሊሰጥ በፍቅር ሊሆን ይገባዋል። ይህም ማለት የሚያደርገው ሁሉ ሌሎችን ለመጥቀም እንጂ እራሱን አግባብነት በሌለው ሁኔታ ወይም ከእግዚአብሔር ሃሳብ ውጪ ለመጥቀም ታስቦ መሆን የለበትም ወይም በሌላ አነጋገር የሌሎች መጠቀምን የእራሱ ጥቅም አድርጎ መቁጠር አለበት፤ እርሱን የሚጠቅም እና የእርሱን ጥቅም የሚያስጠብቅ ግን እግዚአብሔር ነው። ያለ ፍቅር የሚሰጥ አገልግሎት በስግብግብነት ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ የማያሰጥ አክሊል የማያስገኝ ስለሆነ ከንቱ ለአገልጋይ ብድራት የሌለው ነው።

በእግዚአብሔር ፍቅር የተማረከ እና በእግዚአብሔር ፍቅር ለመኖር የወሰነ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየው የሚችል በሰማይም በምድርም ምንም ነገር የለም። ሮሜ 8:35-39 የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ታላቅ ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፤ እንዲሁም ነን። ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም። 1 ዮሐ 3:1-2 ሆኖም ግን እኛ ከቀን ስለሆንን የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኖራለን፤ ባልንጀሮቻችንን በመውደዳችን የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ውስጥ እንዳለ ይታያል። 1 ተሰ 5:8

ይህ መለኮታዊ ፍቅር ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ደኅንነት በመስቀል ላይ በመሰቀል የሰዎችን ኃጢአት በፅድቅ፣ ርኩሰታቸው በቅድስና፣ የሰይጣን ልጅነታቸው በእግዚአብሔር ልጅነት፣ የዘላለም ሞታቸውም በዘላለም ሕይወት እንዲለወጥ ብቸኛ ምክንያት ሆኖ የተገለጠ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን ያከናወነው ከሰዎች አንድ ነገር ተገኝቶ ሳይሆን በእርሱ ዘንድ አንድ ነገር ተገኝቶ ነው፣ ይኸውም ሰው ሊኖራቸው ያለው ፍቅር ነው።

ሰዎች ቢያውቁትም ባያውቁትም የፍቅር ጥማተኞች ናቸው። ፍቅር የሞላበት ሕይወትና አገልግሎትም ከምንም በላይ እነዚህን ጥማተኞች ይስባቸዋል። የእግዚአብሔር ፍቅር በክርስቶስ ኢየሱስ ከማመናችን የተነሳ በእኛ ዘንድ ያለ በመሆኑ ይህ ፍቅር በሙላት ቢገለጥ ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ መንግሥት መሳብና ማምጣት እንዲሁም የፍቅር ጥማታቸውን ማርካት የሚችል ታላቅ የፍቅር ኃይል ይለቀቃል።

"እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ሰማንም ሰዳ ስደኮርባችሁ፣ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና። አታመንዝር፣ አትግደል፣ አትስረቅ፣ በውሸት አትመስክር፣ አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ፡- ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል። ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።" ሮሜ 13:8-10

2. ደስታ

ይህ መለኮታዊ ደስታ ከመንፈስ ቅዱስ መገኘት የተነሣ የሚገኝ ደስታ ነው። ክርስቲያን አንድ ጥሩ ነገር ሲያገኝ የሚያገኘው ዓይነት ደስታ አይደለም። ይልቁኑ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ከማድረጉ የተነሣ በውስጡ በመንፈስ ቅዱስ የሚፍለቀለቅ እና በረከቶችን በማጣትም ይሁን በማግኘት የማይገደብ ነው። ስለሆነም አንዳንድ ጊዜ የማያስደስቱ ሁኔታዎች ቢያጋጥሙት እንኳ ከመንፈስ ቅዱስ በሚቀበለው ደስታ መመላለስ ይችላል። ሁኔታዎች ተለዋዋጭ በመሆናቸው እግዚአብሔር ሁኔታዎችን ለውጦ የሚያሳዝኑ ሁኔታዎችን በማሳለፍ የሚያስደስቱ ሁኔታዎችን በማምጣት በደስታ ላይ ደስታ እስኪሰጠን ባለንበት ሁኔታ ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ መቀበል እንችላለን።

በመንፈስ ቅዱስ መደሰትም ይሁን ዙሪያው በከበበው ደስታን የሚሰርቁ ሁኔታዎች ማዘን የክርስቲያኑ ምርጫ ነው። በሀዘን ስሜት በመዋጥ በዓለም የሀዘን ስሜት ላለመመላለስ እና ለመደሰት መወሰን ይችላል። አሁን ባለበት ሁኔታ ከጌታ ኢየሱስ የተነሳ መደሰት ይችላል። ማዘን አለብህ ብለው ሊያሳዝኑ ድምፃቸውን አውጥተው የሚናገሩትን ነገሮች ሁሉ አለመታዘዝ ይችላል። እግዚአብሔር በዚህኛው ዓለምም ይሁን በሚመጣው ዓለም ከእርሱ ሊያስወግዳቸው ያሉ ጊዜያዊ ነገሮች መሆናቸውን መረዳት አስፈላጊ ነው።

ነገ ሳይሆን ዛሬ መደሰት መጀመር አለብን። ደስታውን በሆነለት ነገር የሚመሠርት ክርስቲያን እንኳን ጌታ ኢየሱስን እንደ የግል አዳኙና ጌታው አድርጎ በመቀበሉ ያገኘውን ዘላለማዊ ማንም ሊነጥቀው የማይችለውን በምድርም በሰማይም ተመሳሳይ የሌለውን ሕይወትና የተትረፈረፈ በረከት ዘወትር በማሰብ መደሰት ይችላል። እግዚአብሔርም ልጆቹን ማስደሰት ስለሚወድ በጊዜው የልጆቹን ደስታ የሚገዳደሩትን ያስወግዳቸዋል። የሆኖ ሆኖ ክርስቲያን እንደ ዓለማውያን የተሳካለት ሲመስል የሚደሰት፣ የወደቀ ሲመስል ደግሞ ወደ ሞት በሚያጣድፍ ሀዘን የሚዋጥ እንዳይሆን ሊጠነቀቅና ከውድቀት የሚያነሳውን አምላኩን እየታመነ ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ የሚለውን ቃል መታዘዙን ልብ ሊለው ይገባል። ፊል 4:4

"የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና።" ሮሜ 14:17

እግዚአብሔር በእርሱ የሚታመኑትን ደስ የሚያሰኝ አምላክ ነው። ጻድቃን ሁልጊዜ በጌታ ደስ እንዲላቸው ታዘዋል። አገልግሎታቸውንም በደስታ ሊያቀርቡ ይገባል። መዝ 63:10፣ ፊል 4:4፣ 2 ቆሮ 9:7፣ መዝ 9:2፣ ሉቃ 1:47-48፣

ከእግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ በኩል የሚሰጠን ደስታ ማንም ሊወስደውና ሊነጥቀን የማይችለው ደስታ ነው። የነገሮች እኛ ባሰብነው ፍጥነት አለመሳካት፣ ስደትና መከራ፣ ልብን የሚያሳዝኑ ገጠመኞች እንኳ ከእኛ ሊነጥቁት አይችሉም። ይህ ደስታ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ቅርበትና ጎብረት ያህል በሕይወታችን ይገለጣል። የዚህ ደስታ ሙላት ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የጎብረታችን ሙላት ወይም በሕይወታችን ካለው ከእግዚአብሔር ሙላት ጋር ይመጣጠናል። 2 ቆሮ 6:10

"እንግዲህ እናንተ ደግሞ አሁን ታዝናላችሁ፣ ነገር ግን እንደገና አያችኋለሁ፣ ልባችሁም ደስ ይሰኛል፣ ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም።"

ዮሐ 16:22፣ ፅን 3:16-18

". . . በመከራችን ሁሉ ደስታዬ ከመጠን ይልቅ ይበዛል።" 2 ቆሮ 7:4

ጻድቃን ምርኮአቸው ሲመለስ፣ እግዚአብሔር ታላቅ ነገር ሊያደርግላቸው፣ የእግዚአብሔር ቃል ሲመጣላቸው፣ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን ስታደርግ፣ ጋጢአተኞች ከክፉ መንገዳቸው ወደ እግዚአብሔር ዘወር ሲሉ ይደሰታሉ። ይህም ሁሉ ደስታ ከጌታ የተሰጣቸው ነው። ነገር ግን ከዚህ ሁሉ ከሚገኘው ደስታ ይልቅ የደስታ ሕይወታቸው በስራው በጌታ በመደሰት የተመሠረተ ሲሆን ይገባዋል። መዝ 1:2፣ ሉቃ 10:20፣ ምሳ 13:19፣ 1 ተሰ 1:6

"እግዚአብሔር የጽዮንን ምርኮ በመለሰ ጊዜ
እጅግ ደስተኞች ሆንን።
በዚያን ጊዜ አፋችን ደስታን፣
አንደበታችንም ሐሤትን ሞላ፣
በዚያን ጊዜ በአሕዛብ ዘንድ፣

እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን አደረገላቸው ተባሉ።
እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን አደረገልን፣
ደስም አሰን።"
መዝ 125:1-3፣ መዝ 118:162፣ መዝ 13:10፣ ሉቃ 15:31-32

ደስታን ለእግዚአብሔር በዝማሬ፣ በዕልልታ፣ በምስጋና መግለጥ ይቻላል። ያዕ 5:13፣ መዝ 117:14-15 ደስታችን ፍጹምና ሙሉ እንዲሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እግዚአብሔር ሀዘንና ትካዜን በደስታ የሚለወጥ አምላክ ነው። እዚህ ላይ ሀዘንና ትካዜ የመንፈስ ፍሬ እንዳልሆኑ ልብ በል። ዮሐ 15:11

ደስታችን ፍጹም እንዲሆን ግን ደስታችንን ለመስረቅ በዙሪያችን የከበቡንን ነገሮች እግዚአብሔር እንዲያነሳ የጌታ ምሕረትና ቸርነት እንዲለቀቅልን መጸለይ ይኖርብናል።

"ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።" ዮሐ 16:24

"የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው. . . በሰመድ ፈንታ ለከሲልን፣ በልቅሶም ፈንታ የደስታ ዘይት፣ በጎዘንም መንፈስ ፈንታ የምስጋና መጎናጸፊያ አሰጣቸው ዘንድ ልኮኛል።" ኢሳ 61:1-3፣ መዝ 44:7-8፣ መዝ 67:3፣ ዮሐ 17:13

እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት መትጋት ይጠበቅብናል። ብዙ ጻድቃን እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተው አልፈዋል። 1 ዮሐ 3:22

"አምላክሽ እግዚአብሔር በመካከልሽ ታዳጊ ኃይል ነው በደስታ በአንቺ ደስ ይሰዋል፣ በፍቅሩም ያርፋል፣ በእልልታም በአንቺ ደስ ይሰዋል ይባላል።" ሶፎ 3:17፣ ቆሳ 1:12

የጻድቃን ተስፋቸው ደስታ ነው። በሚያስለቅሱ ሁኔታዎች ውስጥ ቢሆኑ እንኳ በውስጣቸው በጌታ መደሰት የሚችሉ ሲሆኑ ከፊት ለፊታቸው ደግሞ የእግዚአብሔር ጉብኝት ይዞት የሚያመጣው ደስታቸውን ፍጹም የሚያደርግ ደስታ ይጠብቃቸዋል። ምሳ 10:28፣ መዝ 125:5-6፣ 1 ጴጥ 1:8-9

"ከብሬ ትዘምርልህ ዘንድ ዝምም አንዳትል
ልቅሶዬን ለደስታ ለወጥህልኝ፣
ማቄን ቀደድህ ደሰታንም አስታጠቅኸኝ
አቤቱ አምላኬ ለዘላለም አመሰግንሃለሁ።" መዝ 29:11-12

በንግግራቸው የሰውን ልብ የሚያሳዝኑና የሚያቆስሉ ሰዎች እንዳሉ ግልፅ ነው። ከጠቢብ የጻድቅ አንደበት ግን ሰውን ደስ የሚያሰኝ፣ ሕይወት የሚሰጥ፣ ከክፉ መንገድ የሚመልስ፣ ፈውስ የሆነ ቃል ይንጠባጠባል።

"የጻድቅ ከንፈሮች ደስ የሚያሰኝ ነገርን ያውቃሉ፣
የኀጥአን አፍ ግን ጠማማ ነው።" ምሳ 10:32፣ ምሳ 12:32

ጻድቅ ሰዎችን ሁሉ ደስ ማሰኘት ቢፈልግም አንዳንድ ጊዜ በስንፍና በኃጢአት የሚደሰቱ ሰዎች በጻድቁ ላይ የሚያዝኑበት ጊዜ አለ። ጻድቅም ሰውን ከማስደሰት እግዚአብሔርን ማስደሰት ሊመርጥ ይገባል።

"ልብ ለሌለው ሰው ስንፍና ደስታ ናት
አስተዋይ ግን አካሄዱን ያቀናል።" ምሳ 15:21

"ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኝለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም።" ገላ 1:10

የክርስቶስ ወንጌል ተሰብኮለት የተቀበለ ሕዝብ በደስታ ይሞላል። የጻድቃን ልማት ወይም አገልግሎትም ሕዝብን ያስደስታል። ጻድቃን ለቤተሰባቸውም ደስታ ናቸው። ምሳ 23:24-25፣ ምሳ 17:21፣ ምሳ 10:1፣ ምሳ 11:10፣የሐዋ. 8:5-8

ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ ደስታ ኃይልን ይሰጣል፣ ፊትን ያበራል፣ እንደ ግብጥ ነው። ነህ 8:10፣ ምሳ 15:15፣ መዝ 19:5 የእግዚአብሔር ቃል በጠላቶቻችን ወይም ለእኛ ክፉ በሚመኙ ሰዎች ውድቀት እንዳንደሰት ያስጠነቅቀናል። የምንደሰትበት ነገር የሌለ በሚመስልበት ሰዓት እንኳ በውስጣችን ካለው የእግዚአብሔር መንፈስ ደስታ መምዘዝና መደሰት እንችላለን። ምሳ 24:17-18

የእግዚአብሔር ደስታ ከሀዘን ይጠብቀናል። ሀዘን በሽታን ከማምጣት አንስቶ እየከፋ ከሄደ ጤንነትን ከማወክ አልፎ ከሰዎችና ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት እንኳ ያበላሻል። ደስታችን ፍጹም እንዲሆን ስንዘረጋ ደስታችንን ሁልጊዜ በእግዚአብሔር እናስደግፍ፣ ይህም ክፉውን ቀን አሳልፈን እግዚአብሔር ለጻድቃን ያዘጋጀው መልካም ቀን እንድንደርስ የሚያስችል ኃይል ይጨምርልናል። መቼም ቢሆን በጌታ ያለህን ደስታ ከሚነጥቁ ከማንኛውም ነጣቂዎች ጠብቅ። ከነጣቂዎቹ አንዱ ሰላምን የሚያደፈርሱ ሁኔታዎች ናቸው፣ ሰላም በሌለበት ደስታ የለምና። ደስታን ለመጠበቅ ሰላምን መጠበቅ የሚያስፈልግ ሲሆን ከጌታ የምናገኘውን ሰላም በተመለከተ ከታች እንማራለን።

3. ሰላም

እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነው፣ ጌታ ኢየሱስም የሰላም አለቃ ነው።
ሰላም፣ ፀጥ ያለና የተረጋጋ፣ ከፍርሃትና ከሁከት የፀዳ ልብ ነው። ፀጥ ያለ ወይም የተረጋጋ ከግጭትና ከረብሻ የፀዳ አእምሮም ነው።

"ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ፣ የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል።" ፊል 4:9

"የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል።"
ሮሜ 16:20

"ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፣ አስቀነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፣ ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።" ኢሳ 9:6

እግዚአብሔር ሲናገር ለሕዝቡ ሰላምን ይናገራል፣ ይህን ሰላም የተሞሉም ሰላምን ይናገራሉ። መዝ 84:8፣ ዮሐ 16:3፣ ኤፌ 1:2፣ ፊል 1:2፣ ዮሐ 20:19፣ ዮሐ 20:26

እግዚአብሔር አእምሮንና ልብን የሚገዛ ሰላም ክርስቲያን እንዲሞላ ይፈልጋል። እግዚአብሔር በመንፈሱ በቀጥታ የሚሰጠው ሰላም የዓለምን ዓይነት ውጫዊ ብቻ የሆነ ሰላም አይደለም፣ በከፍተኛ ስደት፣ መከራና ችግር ላይ ሆነን እንኳ ፀጥ ያለና የተረጋጋ ልብና አእምሮ ባለቤት የሚያደርግ ነው። ሆኖም ግን የሚያውኩን ነገሮች ወደ እኛ ሲመጡ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር ለእግዚአብሔር በማሳወቅ ከእኛ ማስወገድ እና የነገር ሁሉ ገዥና ተቆጣጣሪ እግዚአብሔር መሆኑን የሚረዳን አእምሮን ይጠይቃል።

". . . የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ. . . " ቆሳ 3:15

"ሰላምን እተውላችኋለሁ፣ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፣ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም። እኔ እሄዳለሁ ወደ እናንተም እመጣለሁ አንዳልኳችሁ ሰማችሁ።" ዮሐ 14:28

"በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ። አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።" ፊል 4:6-7

ሀ. የሰይጣን የማወክ ጥቃት ሲሰነዘርብህ ላለመታወክ መወሰንና ሁከቱን መቃወም ያለብህ አንተ መሆንህን አትዘንጋ።

ለ. የእግዚአብሔር ሰላም በውስጥህ እንዳለ በእምነት መቀበልና የክርስቶስ ሰላም በልብህ እንዲገዛ መፍቀድ ትችላለህ።

ሐ. ስለ ሁኔታዎች ሰይጣንና ሰዎች የሚናገሩትን አምኖ መረበሽ ወይም እግዚአብሔር የሚናገረውን ሰምቶ በእግዚአብሔር ሰላም መሞላት ምርጫው የአንተ ነው።

"የሚሰማኝ ግን በአርጋታ ይቀመጣል፣
ከመከራም ሥጋት ያርፋል።" ምሳ 1:33

ኃጢአት ሰላምን ያደፈርሳል፣ አንድን ሰው ከእራሱ ጋር ከሌላውም ጋር ያጋጫል፣ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር ያጋጫል፣ የግለሰብንና የሀገርን ሰላም አውኮ ጦርነትን ያነሳሳል።

"ኢዮራምም ኢዩን ባየ ጊዜ፦ ኢዩ ሆይ፣ ሰላም ነውን? አሰ። አርሱም፦ የእናትህ የኤልዛቤል ግልሙትናዋና መተትዋ ሲበዛ ምን ሰላም አስ? ብሎ መለሰ።"
2 ነገ 9:12

እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አካሄድ የሚሄደውን ሰው እግዚአብሔር ከጠላቶቹ ጋር እንኳ ሰላምን ሊሰጠው ይችላል። ጠላት ወደ ወዳጅነት ሁልጊዜ ይለወጣል ማለት ባይሆንም ጌታ ጠላት የነበረውን ሰው ግን ወዳጅ ሊያደርገው ይችላል። ጠላት ወዳጅ መሆን የሚጀምረው ግን አብዛኛውን ጊዜ ጌታ በአንተ

ከሠራው ሥራ የተነሳ እንጂ ጠላትህ መንፈሳዊ ሰው ከመሆኑ የተነሳ አይደለም። ምሳ 16:17 በሰላም መናገር በማይችሉ ሰዎች ውስጥ ተንኮል ታስሯል። ይህ ተንኮል የተመቻቸ ጊዜ ሲያገኝ ይፈታል። ዘፍ 37:4፣ ምሳ 12:20 ጌታም ተንኮለኞች በተንኮላቸው እንዲያዙ ያደርጋል።

የእግዚአብሔር ሰላም የጽድቅ ፍሬን ያፈራል። ዕብ 12:11 ሕይወትን የሚፈቅድና በጎ ዘመንን ማየት የሚፈልግ ሰው ሰላምን መከተል ይኖርበታል። መዝ 33:14 የእግዚአብሔርን ቃል የሚወዱና የሚከተሉም ሰላማቸው ብዙ ነው። መዝ 118:165፣ መዝ 36:1 ክፉዎች ግን የልብ ሰላም የላቸውም።

"ጥል ባለበት ዘንድ እርድ ከሞላበት ቤት
በጸጥታ ደረቅ ቁራሽ ይሻላል።" ምሳ 17:1

"የሰላምም ጌታ ራሱ በሁሉ መንገድ ዘወትር ሰላምን ይስጣችሁ። ጌታ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።" 2 ተሰ 3:16

4. ትዕግስት

እግዚአብሔር ታጋሽ አምላክ ነው። ትዕግሥት የሚያስቆጡ፣ የሚያዘገዩ ነገሮች ሲያጋጥሙ እራስን ማስታገሥ፣ ሁኔታዎችንና ነገሮችን መሸከም፣ ተፈላጊውን ነገር መጠበቅና ጊዜ መስጠት ነው። ዘጸ 34:6-7 ትዕግሥት ከምሕረት ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው። ምሕረት የትዕግሥት ኃይል ነው። ምሕረት ማድረግ የሚችል ለመታገሥ አያዳግተውም። 2 ጴጥ 3:9 ክርስቲያን ትዕግሥትን ሊለብስ፣ በትዕግሥት ሊመላለስ ይገባዋል። ይህንንም በደስታ እንጂ ጥርስን በማንገጫገጭ ሊያደርገው አይገባም። ሮሜ 12:12፣ ቆላ 1:11፣ 2 ጢሞ 2:24፣ 2 ጢሞ 4:2

2 ቆሮ 6:3-10ም ስለ ትዕግሥት ይናገራል። ይህ ምንባብ የጌታ ኢየሱስ አገልጋይ እንዴት ትዕግሥት የተሞላበት ሕይወት ሊኖረው እንደሚገባ ይገልጣል። አስተዋይ ሰው ታጋሽ ነው። ትዕግሥተኛ ደግሞ ጠብን ጸጥ የሚያሰኝ ኃይል አለው። ትዕግሥተኛ ከኃይል ሰው ይሻላል። ምሳ 14:17፣ ምሳ 15:18፣ ምሳ 16:32፣ ምሳ 25:15 በእግዚአብሔር ፊት ጊዜ የሚወስድ፣ ቆይታ በትዕግሥት የሚያደርግ ከእግዚአብሔር መልስን ይቀበላል። ችኩል ግን መልሱን ሳይቀበል ከነጥያቄው ከእግዚአብሔር ፊት ይወጣል። መዝ 39:1፣ ዕን 2:1

"እነሆ፣ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ አንደ ታገሠ ሰምታችኋል፣ ጌታም እንደፈጸመለት አይታችኋል፣ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና።" ያዕ 5:11

"እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፣ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፣ ይሮጣሉ፣ አይታክቱም፣ ይሄዳሉ፣ አይደክሙም።" ኢሳ 40:31

መከራ ትዕግሥትን ያስተምራል ሆኖም ግን በትዕግሥት መልሶ መከራን የሚያልፍ ከፊት ለፊቱ ያለውን ክብር ያገኘዋል። ሮሜ 5:3፣ ዕብ 5:8 ዕብ 12:2

"በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኀዘንን ቢታገሥ ምስጋና ይገባዋልና። ኃጢአት አድርጋችሁ ስትገሰሙ ብትታገሡ፣ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ፣ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል።" 1 ጴጥ 2:19-20

ትዕግሥት የጎደለው ሰው በእምነት አይጸናም፣ ወደ ኋላም ያፈገፍጋል። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ሊታገሥ አይቻለውምና። ሰው ትዕግሥት የሚጎድለው

በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል መጠራጠር ሲጀምር ነው። በእግዚአብሔር ተስፋ የሚያደርግ እርሱ ትዕግሥትን ያደርጋል።

"አሁንስ ተስፋዬ ማን ነው? እግዚአብሔር አይደለምን?
ትዕግሥቴም ከእንተ ዘንድ ነው።" መዝ 38:7

"የማናየውን ግን ተስፋ ብናደርገው በትዕግሥት እንጠብቀዋለን።"
ሮሜ 8:25፣ ዕብ 12:20፣ ዕብ 10:36-39

"ትዕግሥተኛ ሰው ብዙ ማስተዋል አለው፣
ቁጡ ግን ስንፍናውን ከፍ ከፍ ያደርጋል።" ምሳ 14:29

5. ቸርነት

እግዚአብሔር ቸር ነው፣ መንገዱም የቸርነት መንገድ ነው፣ በሥራውም ሁሉ ቸር ነው። ቸርነት የሌሎችን ፍላጎት ከእራስ አስቀድሞ ማሟላት ነው።

"እግዚአብሔር ቸር ቅንም ነው፣
የእግዚአብሔር መንገድ ሁሉ ቸርነትና እውነት ነው"
መዝ 24:8፣10 ፣ መዝ 144:17፣ መዝ 99:5፣ ፊል 2:3-4

እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ለሰው ያለውን ቸርነት አሳይቷል። ኤፌ 2:4-7 ቸርነት እራሱን በርኅራኄና ሀዘኔታ ይገልጣል። ይህ ቸርነትና ርኅራኄ የተሞላ ሀዘኔታ በክርስቶስ ኢየሱስ አገልግሎት ጊዜ ተገልጧል።

"ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፣ አረኝ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው።" ማቴ 9:36

የጌታ ቸርነት ጻድቃንንም በቤቱ ለዘላለም ያኖራል። ይህ ቸርነቱ የሰዎችን ሕይወት ከውርደትና ለማኝነት ይጠብቃል፣ ይከላከላል፣ ከዚያም አልፎ ያበረታል። መዝ 22:6፣ መዝ 24:7

"በአንተ ለሚታመኑ በሰው ልጆች ፊት ያዘጋጀሃት
ለሚፈሩህም የሰወርሃት፣
ቸርነትህ እንደምን በዛች!" መዝ 30:19፣ መዝ 39:11፣ ምሳ 20:28

እግዚአብሔር መልካም ነገርን ሲያደርግልህ፣ ከተቀበልከው ቸርነት ቤተሰብህን፣ ዘመዶችህን፣ ጓደኞችህን፣ ሌሎችን አስብ። ይህንንም በእግዚአብሔር ቸርነት በመታመን በደስታ ፈጽመው፤ የእግዚአብሔር ቸርነት አያቋርጥምና። ለሚያመሰግኑም ለማያመሰግኑም ለመልካሞችም ለክፉዎችም ቸር እንሁን። በእግዚአብሔር ቸርነት የታመነ ለድሀ ቸርነትን ያደርጋል።

"ስቅዱሳን በሆነው አገልግሎት እንዲተባበረ ደህን ቸርነት በብዙ ልመና ከእኛ ይሰምኑ ነበር፣ አስቀድመው በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለጌታ ለእኛም ሰጡ እንጂ እንዳሰብን አይደለም።" 2 ቆሮ 8:4-5፣ መዝ 12:5

"ዳዊትም፦ ስለ ዮናታን ቸርነት አደርግለት ዘንድ ከሳኦል ቤት አንድ ሰው ቀርቶአልን? አለ።" 2 ሳሙ 9:1፣ 1 ሳሙ 30:26፣ መዝ 17:50

"ለድሀ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል፣
በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል።"
ምሳ 19:17፣ መዝ 111:5፣9፣ ሉቃ 6:32-36

6. በጎነት

እግዚአብሔር በጎ ሲሆን ለሰው ልጅ የሰጠው ስጦታ ሁሉ በጎና ፍጹም ነው። ሰይጣን ለሰዎች የሰጠው በጎ ስጦታ ምንም የለም። በጎነት መልካም የሆነ ነገር ወይም ሁኔታን ይገልጣል።

"የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፣ አትሳቱ። በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፣ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ።" ያዕ 1:16-17

"እግዚአብሔርም በጎ ነገርን ይሰጣል
ምድራችንም ፍሬዋን ትሰጣለች።" መዝ 84:12

"በበጎ በረከት ደርሰህበታልና
ከክብር ዕንቁ የሆነ ዘውድን በራሱ ላይ አኖርህ።" መዝ 20:3፣ ሉቃ 6:8-11

የእግዚአብሔር ሕግ በጎ ነው። ሮሜ 7:12 እግዚአብሔር ልጆቹ ልንሆን የወሰነው በበጎ ፈቃዱ ነው። ክርስቲያንም ወንጌል የሚሰብከውና እግዚአብሔርን የሚያገለግለው ከበጎ ፈቃዱ የተነሣ ነው። ኤፌ 1:5፣ ፊል 1:15፣ 2 ቆሮ 8:12 ይህ በጎነት በኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት በማቴ 21:12-14 ባለው ክፍል ይታያል። በዚህ ክፍል ኢየሱስ ክርስቶስ

ሀ. ቤተ መቅደሱን አጸዳ
ለ. ዕውሩንና አንካሳውን ፈወሰ
ሐ. መልካሙ ኢየሱስ ክፉውን ነገር በሥልጣንና በድፍረት ከመቅደስ በማስወገድ ለሌሎች በጎ ነገር በማድረግ ቅዱስ፣ ጥሩ፣ መልካም ምግባር

ያለበትን ነገር በማድረግ ምሳሌ የሚሆን ነገር በቤተ መቅደሱ ለነበሩ አስቀርቶላቸዋል።

ከክርስቲያን አንደበት ሊወጣ የተገባው በጎ ቃል ነው። ከዚህም በተጨማሪ በጎ ነገር ለማድረግ እና ከበጎ ነገር ጋር ለመተባበር የተዘጋጀ መሆን አለበት። ሆኖም ግን የሚያደርገው ነገር በጎ ቢሆንም በመለኮታዊ ጥበብ ሊደረግ ይገባዋል። አንዳንድ ጊዜ በጎ ነገር እየተደረገ በመለኮታዊ ጥበብ ስለማይደረግ የተፈለገው ውጤት ሳይገኝ ይቀራል። ኤፌ 4:29፣ ሮሜ 12:9

". . . ነገር ግን ለበጎ ነገር ፕበበኛች ለክፉም የዋሆች እንድትሆኑ እወዳለሁ።"
ሮሜ 16:19

"ወዳጅህን፣ ሂድና ተመለስ ነገ እሰጥሃለሁ አትበለው በጎ ነገር ማድረግ ሲቻልህ።" መዝ 3:28

ክርስቲያን፡-

ሀ. በጎ የሆነውን ሊያደርግ ይገባዋል

"እንግዲያውስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ደልቁንም ለጋይማኖት ቤተሰቦች መልካም እናድርግ።" ገላ 6:10

"ገዥዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሪ አይደሉምና። ባለሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል፣ ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና።"
ሮሜ 13:3

ለ. በጎ ሥራ መሥራት አለበት

"ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል፣"
ሮሜ 2:10፣ ኢፌ 6:7-8

ሐ. ክፉውን በመልካም (በበጎነት) ማሸነፍ አለበት፡-

"ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።" ሮሜ 12:21

በጎ የሆነ ዘመን አለ። ጻድቅ ክፉውን ዘመን አልፎ በጎውን ዘመን ያያል። በሕይወትህ በጎነት እንደጎደለህ ካለብህ በመንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር በጎነትን ልትሞላና በእግዚአብሔር በጎነት ልትመላለስ እንደምትችል እወቅ። እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የማያቋርጥ በጎነት ስንረዳ ለሌሎች በጎ መሆን አያዳግተንም። እግዚአብሔር ለእኛ ያለው በጎነት የተገለጠልንን ያህል ለሌሎች በጎ እንሆናለን።

"እግዚአብሔርን፡- አንተ ጌታዬ ነህ አልሁ፣
ከአንተ በቀር በጎነት የለኝም።" መዝ 15:2

"ሕይወትን የሚፈቅድ ሰው ማን ነው?
በጎነም ዘመን ለማየት የሚወድድ?
አንደበትህን ከክፉ ከልክል፣
ከንፈሮችህም ሽንገላን እንዳይናገሩ።
ከክፉ ሽሽ መልካምንም አድርግ
ሰላምንም እሻ ተከተላትም።" መዝ 33:12-14

7. እምነት /ታማኝነት/

እምነት በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ KJV ትርጉም Faith የሚለው ቃል ሲሆን ሌላው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም Revised Version እንዲሁም ሌሎች የቅርብ ጊዜ ትርጉሞች እምነት ለሚለው ቃል የተጠቀሙት faithfulness የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ነው። Faithfulness የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል በአማርኛ በቀጥታ ስንተረጉመው ታማኝነት ወይም እምነት የሚጣልበት ማለት ነው።

እግዚአብሔር ታማኝ አምላክ ሲሆን በቃሉቹ ሁሉ የታመነ ነው። እግዚአብሔር አይለወጥም።

"እግዚአብሔር በቃሉቹ የታመነ ነው።
በሥራውም ሁሉ ጻድቅ ነው፣"
መዝ 144:14፣ ዕብ 10:23፣ 2 ጢሞ 2:11-13

"እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም" ሚል 3:6፣1 ተሰ 5:24

"ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለም ያው ነው።" ዕብ 13:8

እግዚአብሔር ከታማኝነቱና ታማኝነቱ የማይለወጥ ከመሆኑ የተነሣ ጻድቃን ይታመኑበታል። በእግዚአብሔር የታመኑ ደግሞ ይበረታሉ፣ ትዕግሥትን ያደርጋሉ፣ ኃይላቸውን ያድሳሉ፣ ክበኃነቱ ይቀበላሉ፣ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳ ቢሆኑ በአምላካቸው ለላማቸው ይጠበቃል፣ የተሰጣቸውን መልካም አደራ በመንፈስ ቅዱስ ለመጠበቅ ኃይል ያገኛሉ፣ ወ.ዘ.ተ 2 ጢሞ 1:12፣ መዝ 63:10፣ 2 ጢሞ 1:14

"በእግዚአብሔር የታመኑ
እንደማይታወክ ለዘላለም እንደሚኖር
እንደ ጽዮን ተራራ ናቸው።" መዝ 124:1

"በሰው ከመታመን ይልቅ በእግዚአብሔር ተስፋ ማድረግ ይሻላል"
መዝ 117:8-9

"ከማለዳው ሰዓት ጀምሮ እስከ ሌሊት
ነፍሴ በእግዚአብሔር ታመነች።" መዝ 129:6

"በጋጢስተኛ ብዙ መቅሠፍት አሰበት፣
በእግዚአብሔር የሚታመነውን ግን ምሕረት ይከብበዋል።" መዝ 31:10

ክርስቲያን እግዚአብሔር በእጁ አላልፎ በሚሰጠው ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር እና ለሰው ታማኝ እንዲሆን ይጠበቅበታል። ታማኞችን ደግሞ እግዚአብሔር ከትንሽ ወደ ትልቅ ያሳድጋቸዋል። ሹመትና ዕድገት ለታማኞች ነው። ማቴ 25:14-30ን በጥንቃቄ አንብቡው።

ክርስቲያን፦

ሀ. ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ታማኝ መሆን አለበት።

ለ. እግዚአብሔር ለሰጠው ቤተሰብና አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ታማኝ መሆን አለበት።

ሐ. የሌሎችን ሰዎች አደራ መጠበቅ አለበት። ይህም ከሌሎች ሰዎች የተበደረውን ማንኛውንም ነገር በጥንቃቄ ተጠቅሞ ከመመለስ እስከ ሌሎች

ሰዎች እርሱ ጋር በአደራ ያስቀመጡትን እስኪወስዱት እስከ መጠበቅ፣ የተሰጠውንም ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ እስከ መወጣት ነው።

"ከሁሉ በሚያንስ የታመነ በብዙ ደግሞ የታመነ ነው፣ ከሁሉ በሚያንስም የሚያምፅ በብዙ ደግሞ ዓመፀኛ ነው። እንግዲያስ በዓመፃ ገንዘብ ካልታመናችሁ፣ እውነተኛውን ገንዘብ ማን አደራ ይሰጣችኋል? በሌላ ሰው ገንዘብም ካልታመናችሁ፣ የእናንተን ማን ይሰጣችኋል?" ሉቃ 16:10-12

መ. በምድር ላይ እግዚአብሔር ታማኝ አድርጎ ቆጥሮ በሰጠው በማንኛውም ነገር ላይ ታማኝነትን ማሳየት አለበት። የጊዜ አጠቃቀሙ እንኳ በታማኝነት ምን ያህል እየተመላለሰ እንደሆነ ያሳያል።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአገልግሎት ኃላፊነትን ሲሰጡ የሰዎችን ጸጋ ብቻ ሳይሆን ታማኝነታቸውን ጭምር ፈትነው ሊሰጡ ይገባል። ሆኖም ግን አንዳንድ ጊዜ ታማኝ አድርገን የቆጠርናቸው ሰዎች በእኛ ላይ ሲነሡ ልባችንን በመጠበቅ እኛ እራሳችን ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ታማኞች እንደ ሆንን እንቁም። 1 ጢሞ 1:12፣ 2 ጢሞ 2:2፣

"ደግሞም የሰላሜ ሰው የታመንሁበት
እንጀራዬን የበላ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ።"
መዝ 40:9፣ ምሳ 25:19

"እንኪያስ ምግባችሁን በጊዜው ይሰጣችሁ ዘንድ ጌታው በቤቱ ሰዎች ላይ የሾመው ታማኝና ልባም ባሪያ ማን ነው? ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል። ያ ክፉ ባሪያ ግን፣ ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ፣ ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፣ የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም

ሰዓት ይመጣል፣ ከሁለትም ይሰነጥቀዋል፣ እድሉንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፣ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።" ማቴ 24:45-51

8. የውሃት

የውሃት ገርነት፣ የዋህነት ሲሆን ትህትናንና የሚማር ልብን ያሳያል። የሚማር ልብ ማለት እግዚአብሔር ወደ እኛ የሚያመጣቸውን ነገሮች እግዚአብሔር ከእኛ በላይ እንደሚያውቅ በማወቅ ያለ ክርክርና ተቃውሞ ወይም ማጉረምረም መቀበል ነው። ጌታ ኢየሱስ የዋህ እንደ ሆነና የዋህነትንና ትሕትናን ተከታዮቹ ከእርሱ እንዲማሩ ነግሯቸዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ የዋህነትም ነግሷል።

"ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፣ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፣ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።"
ማቴ 11:29-30፣ መዝ 44:4

እግዚአብሔር የዋሆችን በመንገዳቸው ይመራቸዋል። ክፉዎች ግን የእግዚአብሔር መንገድ ይጠፋባቸዋል። የዋሆች ምድርን ይወርሳሉ፣ የወረሰ ደግሞ ማውረስ ይችላል። የዋሆች በእግዚአብሔር ክብር የተሞላ ሰው ሲያዩ ይደሰታሉ። ማቴ 5:5፣7-8፣ መዝ 36:11፣ መዝ 33:2፣ መዝ 24:9

ፍጹም ክፉ ነገር ሲያጋጥመው በየዋህነት በክፉ ፈንታ መልካም ሊመልስ ይገባዋል። የዋህነት ከክፉና አስደንጋጭ ነገር ይጠብቃል፣ ሞገስን፣ ባለጠግነትን፣ ክብርን፣ ሕይወትንም ያስገኛል። በየዋህነት መመላለስ ትጋትን ይጠይቃል። ሮሜ 12:16፣ ሮሜ 16:19፣ መዝ 24:21፣ ምሳ 3:34፣ ምሳ 14:30፣ ምሳ 18:12፣ ምሳ 22:4

"እቤቱ፣ እኔ በየውሃቴ ሄጻለሁና ፍረድልኝ፣
በእግዚአብሔርም አምናለሁና አልናወጥም።
. . . እኔ ግን በየውሃቴ ሄጻለሁ፣
አድነኝ ማረኝም።" መዝ 25፡1፣11

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዲያብሎስ ሕያዋን ሆነው የተያዙ ተቃዋሚዎቻቸውን በየዋህነት ሊቀጡ፣ የእግዚአብሔርንም ሕዝብ በክርስቶስ የዋህነትና ገርነት ሊመክሩ ይገባል። 2 ጢሞ 2፡25-26

"እኔም ራሴ ጳውሎስ፣ በአናንተ ዘንድ ፊት ሰፊት ሳለሁ ትሑት የሆንሁ፣ ከአናንተ ግን ብርቅ የምደፍራችሁ፣ በክርስቶስ የዋህነትና ገርነት እመክራችኋለሁ።"
2 ቆሮ 10፡1

ያዕ 1፡21፡- "ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን በውስጣችሁም የተተከለውን ቃል በየዋህነት ተቀበሉ" ይላል። በገላ 6፡1 ደግሞ የውሃት ቸርና አፍቃሪ የሆነ ትሑት መንፈስን በሚገልጽ መልኩ ቀርቧል።

"ወንድሞች ሆይ፣ ሰው በማንኛውም በደል ስንኳ ቢገኝ፡- መንፈሳውያን የሆናችሁ አናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውጋት መንፈስ አቅኑት አንተ ደግሞ እንዳትፈተን አራስህን ጠብቅ።"

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡-

ሀ. መንፈሳዊ የሆነ በማንኛውም በደል የተገኘውን ወንድሙን ማቅናት እንደሚችል ያሳያል። ብዙ ክርስቲያኖች የሌሎችን ክርስቲያኖች ጉዳት እያዩ እንዳላዩ ሆነው ያልፋሉ፣ ሊረዷቸው ሊችሉና ሊገባቸው።

ለ. "አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ" ይላል። ይህም ተመሳሳይ ችግር ውስጥ እንዳትገባ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን አራስህን ከሌሎች የበላይ በማድረግ አንተ እንደዚያ ወንድም ዓይነት ችግር እንደማይደርስብህ አድርገህ አትቁጠር፣ ብትቆጥር ግን እንደዚያ ዓይነት ችግር ገና ሳይደርስብህ አሁኑኑ የመታበይ ወይም በአራስ የመመካት ችግር እንዳለብህ ያሳያል።

በተጠራህበት ጥሪ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ለመመላለስ በየውሃት መመላለስን ይጠይቃል።

"እንግዲህ በጌታ አስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ አስምናችኋለሁ፣ በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም እርስ በእርሳችሁ በፍቅር ታገሡ፣ በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።"
ኤፌ 4፡1-3

ይህም የሚከተሉትን ቁም ነገሮች ያስገነዝበናል፡-

ሀ. ከሌሎች ክርስቲያኖች ያለህ አንዳንድ የተለየ ከመሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የማይገናኝ አስተሳሰብ ከክርስቲያኖች ጋር ለመጋጨት ምክንያት ሊሆን አይገባም። እንደ ተሰጠህ ራዕይና ጸጋ ስትመላለስ ሳትጋጫቸው የሚጋጨህን ክርስቲያኖች ደግሞ በምሕረት በተቃኘ አስተሳሰብ ለጌታ አደራ ስጥ፣ እግዚአብሔር በሁሉም ላይ ጻድቅ ፈራጅ ነውና።

ለ. ሁሉንም እንደምታውቅ አታስብ ወይም ሁሉንም እንደምታውቅ ያህል ለመረማመድ አትሞክር። ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር እንደሆነ በማስተዋል በእግዚአብሔር በመመካት ተመላለስ።

ሐ. ለፍቅር ቦታ ስጥ። የመንፈስ ጎብረትን በሰላም ማሰሪያ ለመጠበቅ እግዚአብሔር ባስቻለህ መጠን ትጋ። ፍቅር የራሱን አይፈልግም፣

በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ፊት አይመካም፣ አይታበይም፣ የማይገባውን አያደርግም። 1 ቆሮ 13:1-6 ከክፋት ጋር ከተጣበቁ ሰዎች ግን ራቅ።

9. እራስን መግዛት

አንዳንድ ክርስቲያኖች ለዚህ ቃል የሚሰጡት ትርጉም የተዛባ ነው። ይህ ቃል በቅርብ ስናየው እራስን ስለ መግዛት እንጂ አንዳንድ ክርስቲያኖች እንደሚያስቡት መንፈስ ቅዱስን ስለ መግዛት አይናገርም፣ እራስን ስለ መቆጣጠረ እንጂ መንፈስ ቅዱስን ስለመቆጣጠር አያመለክትም። በእኛና እግዚአብሔር በሆነው በውስጣችን ባለው መንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ልዩነት በትክክል ልናውቅ ይገባል። አለበለዚያ መንፈስ ቅዱስን ለመግዛት፣ ለመቆጣጠርና ለመምራት ስንሞክር በሕይወታችን የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴን እናጠፋለን፣ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ምሪት አይንቀሳቀስምና። ሆኖም ግን የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በሕይወታችን ጠፍቶ እርሱን እንደ ተቆጣጠርነው ያህል ሊሰማን ይችላል። እርሱ መሪ እንጂ ተመሪ፣ ገዢ እንጂ ተገዢ አይደለም።

ክርስቲያን ለመንፈስ ቅዱስ ሲገዛ በእርሱ መሪነት፣ አስተማሪነት፣ መካሪነት፣ አጽናኝነት፣ ኃይል ሰጪነት፣ ወ.ዘ.ተ ሥር እራሱን ሲያደርግ በሕይወቱ እራስን መግዛት ይገለጣል። ክርስቲያን ለመንፈስ ቅዱስ በመገዛትና እራስን በመግዛት መካከል ያለውን ልዩነት አጥብቆ ካልተረዳ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብሮ ለመሥራት እና መንፈስ ቅዱስ በእርሱ እንዲሠራ እራሱን አሳልፎ ለመስጠት ይቸገራል። ከዚያም በላይ ለመንፈስ ቅዱስ እራሳቸውን አሳልፈው በሰጡት ክርስቲያኖች የሚሠራውን ሲያይ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ተቃዋሚ ሆኖ ለመነሣት ይፈተናል።

ለመሆኑ እራስን መግዛት ምንድን ነው? አግባብነት ከሌላቸው ነገሮች እራስን መከልከል ነው። በመንፈስ ቅዱስና በስሜት መካከል ያለውን ልዩነት ከተረዳን እራስን መግዛት ማለት ሌላው ስሜትን መቆጣጠር መቻል፣ ወይም ስሜትን በተገቢው መንገድ መግለጽ መቻል ነው።

እራስን መግዛት (Self Control ወይም Temperance) ለአንድ ክርስቲያን እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። እራሱን የማይገዛ ክርስቲያን ለሰይጣን ጥቃት እራሱን ክፍት ያደርጋል። ጠላቱም ሲመጣ በተከፈተለት በር በመግባት ብዙ የጥፋት ሥራውን ይፈጽማል። ክርስቲያን ተገቢ ካልሆኑ ነገሮች እራሱን መከልከል የሚችልበትን መለኮታዊ ኃይል ከመንፈስ ቅዱስ መቀበል ይችላል። ሆኖም ግን አሁንም አጥብቆን ልንረዳው የሚገባ ነገር ቢኖር ክርስቲያን እራሱን የሚከለክለው የሚሠራውን ከሚያውቅ ፍጹም ከሆነው ከእግዚአብሔር መንፈስ ሳይሆን ከሰይጣንና ከኃጢአት ነው።

> "ቅጥር እንደ ሌላት እንደ ፈረሰች ከተማ፣
> መንፈሱን የማይከለክል ሰው እንዲሁ ነው።" ምሳ 28:28

በዚህ በምሳ 28:28 ላይ መንፈሱን የሚለው የሰውን መንፈስ እንጂ መንፈስ ቅዱስን አይደለም። ከዚህ በታች እራስህን ልትገዛባቸው ከሚገባቸው ነገሮች ጥቂቶቹ ተዘርዝረዋል።

ሀ. የምታነበውን መጽሐፍና መጽሔት መምረጥ
ለ. የምታያቸውን ፊልሞችና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች መምረጥ
ሐ. የምታስበውን መምረጥ
መ. ጊዜህን በአግባቡ መጠቀም፣ ለምሳሌ፣ ለፀሎትና ለእግዚአብሔር ቃል የተገባውን ጊዜ ወስኖ በአግባቡ ለተወሰነለት ጉዳይ ጊዜውን መጠቀም

ሠ. የእንቅልፍ ጊዜን መወሰን፤ ከመጠን በላይ መተኛት ሰነፍና ዳተኛ ያደርጋልና።

ረ. ምን ያህል እንደምትመገብ መወሰን፤ ከመጠን በላይ በልተህ ሆድህን እንዳይዝህ፤ ይህ በተለይ የምትወደውን ምግብ ስታገኝ ሊያጋጥምህ ይችላል።

ሰ. ገንዘብን በተገቢው ቦታ ማዋል፤ በአንድ በኩል ከቆንቋናነት በሌላ በኩል ከአባካኝነት እራስን መከልከል፡

ሸ. ዘዋሪ ሀሜተኛ በመሆን የሰዎችን ቤትና ኑሮ ከማናጋት እራስን መከልከል፤ ስለ ሰዎች የምትሰጠው ምስክርነት ሁልጊዜ ሚዛኑን የጠበቀና ከምስጢር አባካኝነት የተጠበቀ መሆን እንዳለበት አትዘንጋ።

ቀ. ስሜትህን ለሰዎች በተገቢው መንገድ መግለጽ፤ ከስሜት አልባነት ወይም ፈዛዛነት እንዲሁም ከገደብ የለሽ ስሜታዊነት እራስን መከልከል። ምሳ 17:27

> "እጥብቀህ እንዳትጠግብ እንዳትተፋውም
> ማር ባገኘህ ጊዜ የሚበቃህን ብላ።
> እንዳይሰሰችህ እንዳይጠላህም
> እግርህን ወደ ባልንጀራህ ቤት አታዘውትር። መሳ 25:16-17፤ 1 ቆሮ 9:27

> "ትዕግሥተኛ ሰው ከኃይል ሰው ይሻላል፤
> በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማ ከሚወስድ ይበልጣል።" ምሳ 16:32

እዚህም ጋር ልብ በል፤ በመንፈሱ የሚገዛ እንጂ መንፈስ ቅዱስን የሚገዛ አይደለም። እራሳችንን ባለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈትነን ልናደርግ የተገባንን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ለኃጢአት ከሚጋብዙ ቦታዎች፤ ሥፍራዎች፤ ሁኔታዎች፤ ነገሮች፤ ወ.ዘ.ተ እራሳችንን መከልከል አለብን። 1 ቆሮ 7:5-6

"ስለዚህ፤ ወዳጆች ሆይ፤ ሁል ጊዜ እንደ ታዘዛችሁ፤ በእናንተ ዘንድ በመኖሬ ብቻ ሳይሆን ደልቁን አሁን ስርቅ፤ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ . . . በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል ያለ ነቀፋ የዋሆችም ነውርም የሌለባችው የእግዚአብሔር ልጆች እንድትሆኑ ሳታጉረመርሙ ከፋም ሳታስቡ ሁሉን አድርጉ፤ በእነርሱም መካከል የሕይወትን ቃል አያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ፤"

ፊል 2:12-16

አማኞች የእራሳቸውን መዳን እንዲፈጽሙ ፊል 2:12-16 ያዛል። መዳንን መፈጸም ማለት ምን ማለት ነው? አማኝ መዳኑን የሚፈጽመው በክርስቶስ ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት በማደግ ነው። ስለሆነም መዳንን መፈጸም ማለት በክርስቶስ ሙሉ ሰው መሆን ማለት ነው። ልብ በል፤ መዳናቸውን የሚፈጽሙት በክርስቶስ የዳኑ ወይም የጸደቁ አማኞች ናቸው። ስለሆነም አማኞች መዳናቸውን የሚፈጽሙት ለመጽደቅ ሳይሆን ወደ ሙሉ ሰው ለማደግ ነው። የሆኖ ሆኖ ግን አማኝ በሚሞትበት ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ገና ሕፃን ቢሆንም ወይም ክርስቶስን ፍጹም ወደ መምሰል ቢደርስም መጽደቁና የዘላለም ሕይወት እንዳለው ግን መረሳት የለበትም። ጌታ ኢየሱስ ከእርሱ ጋር በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የነበረው በሕይወቱ ፍፃሜ ላይ በክርስቶስ ያመነው ወንበዴም ገነት እንደሚገባ በሉቃ 23፡ 39-43 ላይ መስክሯል። ጳውሎስም በ1ቆሮ 5፡1-5 የአባቱን ሚስት አግብቶ የነበረው አማኝ የዘላለም ሕይወት እንዳለው በመመስከር ለሠራው ኃጢአት ቅጣት እንዲሆን ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፈርዷል።

ክርስቶስን በመምሰል ለማደግ እየተዘረጋን ክርስቶስን የመሰልነውን ያህል ጌታን እያከበርን የሕይወት ጉዞአችንን እንጓዝ። ክርስቶስን መምሰል ለነገር ሁሉ ይጠቅማል።

- ✓ ሰይጣንና ክፉውን ማወቅ ሞትን ወደ ሰው ልጅ አምጥቷል። አብንና ጌታ ኢየሱስን ማወቅ ደግሞ የዘላለም ሕይወት ነው።

- ✓ የሥጋ ሥራን በማስወገድ የመንፈስ ፍሬን የሚያፈራ አማኝ እግዚአብሔርን እየመሰለ ይመጣል።

- ✓ የእግዚአብሔርም ትዕዛዝ፡- በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ ትእዛዙንም እንደሰጠን አርስ በአርሳችን እንዋደድ ዘንድ ነው።

- ✓ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የእራሱን ሕይወት እንኳ ለእግዚአብሔር ፍቃድ ለመሰዋት የተዘጋጀ መሆን ይጠበቅበታል።

- ✓ የአዲስ ኪዳን ትእዛዝ ባልንጀራህን እንደ እራስህ ውደድ የሚል ነው። ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይህን ብቸኛ እና ሕግ ሁሉ የተጠቀለለበትና የተፈጸመበትን ትእዛዝ ሳይቃረን መተርጉም አለበት።

- ✓ ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።

- ✓ በፍቅር የምትመላለሰው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመተባበር በመንፈስ ለመመላለስ በመምረጥና በመወሰን እንጂ የስሜት ሕዋሳትህን እያደመጥህና ለስሜትህ እየተገዛህ በስሜት እየተመላለስህ አይደለም።

- ✓ ሰይጣን ሌባ እንጂ ሰጪ አይደለም። ቸር ወይም ሰጪ ጌታ ነው።

- ✓ ሰዎች ሁሉ እንዲወዱን ማድረግ ባንችልም፣ ሰዎችን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ በመኖር መውደድ ይቻላል።

ምዕራፍ ሰባት

የሥጋ ሥራን ማስወገድ

ክርስቶስን ለመምሰል አማኝ ክርስቶስን እንዳይመስል የሚያደርገው የሥጋ ሥራ ምን እንሆነና እንዴት ማስወገድ እንደሚችል ማወቅ አለበት። የሥጋ ሥራን በተመለከተ ለአጠቃላይ ግንዛቤ በሚጠቅም መልኩ አጭር ነገር ከታች እንመለከታለን።

1. የሥጋ ሥራ

የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው፤ እርሱም ዝሙት፤ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ ይህንም የሚመስል ነው። ገላ 5፡19-21

ሀ. ዝሙት

አንድ ያላገባ ሰው ከጋብቻ ውጪ የሚፈጽመው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ዝሙት ሲሆን አንድ ያገባ ሰው ከትዳር ጓደኛው ውጪ የሚፈጽመው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ምንዝርና ይባላል። ዝሙትና ምንዝርና ግን በተለዋዋጭነት እንዲሁም ከላይ የቀረቡትን ሁለቱንም ሃሳቦች በመጠቅለል ጥቅም ላይ የሚውሉበት ጊዜ እንዳለ መረዳት አስፈላጊ ነው። ከሥጋ ሥራ ዝሙት በመጀመሪያ መጠቀሱ ከሌሎች የሥጋ ሥራ የከፋ መሆኑን ያሳየናል። ይህንኑ 1 ቆሮ 6፡16-18 ሲያረጋግጥ እንዲህ ይላል፡-

"ከጋስሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ሥጋ እንዲሆን አታውቁምን? ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ ተብሎአልና። ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው። ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።"

ምሳ 6:24፣ ኤፌ 5:5፣ ዕብ 12:16፣ 13፤4፣ 1 ተሰ 4:3ንም ተመልከት።

ለ. ርኩሰት

ሰውነትን እግዚአብሔር ካቀደለት ዓላማ ውጪ መጠቀም ርኩሰት ነው። 1 ተሰ 4:7፣ ራዕይ 21:27፣ ሮሜ 1:24፣ ኤፌ 5:3

ሐ. መዳራት

መዳራት ከትዳር ጓደኛ ውጪና ከትዳር ውጪ ለወሲብ የሚያዘጋጁ ጨዋታዎችን መጫወት ነው። ሮሜ 13:13

መ. ጣዖትን ማምለክ

ከእንጨት ከድንጋይ የተሰሩ አማልክት ሁሉ ጣዖታት ሲሆኑ ከእንዱ አምላክ ውጪ በማንኛውም ስም የሚጠሩ አማልክትን ማመን፣ ማምለክ፣ እውቅና መስጠት ጣዖትን ማምለክ ነው። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ጣዖት ማለት በድንጋይ፣ በእንጨት፣ ወ.ዘ.ተ ተቀርፆ የተሠራ ሰዎች የሚሰግዱለት ምስል ብቻ ሳይሆን በሰዎች አእምሮ ከእግዚአብሔር የበለጠ ገዝፎ፣ አስፈሪና ንጉሥ፣ ባለስልጣን፣ ገንዘብ፣ ወ.ዘ.ተ ሆኖ ያለ ወይም ከእግዚአብሔር በላይ የሚወደድ ሆኖ የተቀመጠ ወይም የተሳለ ማንኛውም ሰብአዊ፣ መላእክታዊ፣ ግዑዝ÷ ገንዘብ፣ ወሲብ፣ ስልጣን፣ ምኞት፣ወ.ዘ.ተ. . .ሁሉ ጣዖት ነው።

በተለይ ባለስልጣን የሆኑ ሰዎች የስልጣናቸውን ወሰን ሊረዱና ከተሰጣቸው ስልጣን ውጪ እንደ ናቡከደናፆር በሰዎች ላይ ወሰን የሌለው ስልጣን ለመጠቀም በመሞከር በእግዚአብሔር ቦታ እራሳቸውን በማስቀመጥ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳይጋጩ ሊጠነቀቁ ይገባል። አንድ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት መሆኑን በማወቅ ከጣዖታት ሁሉ እራሱን መጠበቅ አለበት። በአእምሮውም ከማንምና ከምንም በላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ጎልቶ ሊሳል ይገባዋል። 1 ዮሐ 5:20-21፣ ገላ 1:1። 1ቆሮ 10:14 ወዳጆች ሆይ፡- ጣዖትን ከማምለክ ሽሹ ይላል። ለጣዖት መሰዋት ለአጋንንት እንደ መሰዋት፣ ጣዖትን ማምለክ አጋንንትን እንደ ማምለክ ነው። 1 ቆሮ 10:19-22፣ ዘጸ 20:4፣ ዘሌዋ 26:1፣ ዘዳ 7:25፣ 11:16 አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ውጪ ሌሎችን አማልክትንና ጣዖታትን ሲያመልክ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሲፈራ፣ ሲታዘዝ፣ ወ.ዘ.ተ መንፈሳዊ ምንዝርና እንደ ፈጸመ ይቆጠራል። ሆስ 4:13፣7:14፣ 13:2 ጣዖት አምልኮ መንፈሳዊ ምንዝርና በጌታ ላይ እንደ መፈጸም የሚቆጠረው መመለክ ያለበት እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው።

ሠ. ምዋርት

ከሥጋ የሆነ ምዋርት ክፉ ነገር በሰዎች ላይ እንዲመጣ ከጌታ መንፈስ መልእክት ሳይቀበሉ በክፉ ምኞት በመነሳሳት ከሥጋ የሆነ ክፉ ቃል መናገር ነው። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ምዋርት የሥጋ ሥራ የሆነው ምዋርት ሲሆን በሌላ አገባቡ ምዋርት ከክፉ መንፈስ ተቀብሎ ክፉ ቃል በሰዎች ላይ መናገር ነው። ዘጸ 22:18፣ ዘሌ 19:31፣ 20:6፣ ሚክ 5:12

ረ. ጥል

ጥል ይቅርታ ቢስ ከመሆን የሚመነጭ የስግብግብነት መገለጫ ነው። መጣላት

የተወሰነን ወገን እንደ ጠላት በመቁጠር ማንኛውንም ግንኙነት ማቋረጥና ክፉ መመኘት ነው። ዘሌዋ 19፣ምሳ 10:12፣ 15:17፣ 1ዮሐ 2:9 አማኝ በክፉ መንገድ ከሚሄዱ ሰዎች እንዲርቅ በጌታ ቃል ተመክሯል። ሆኖም ግን መራቅ ካለበትና መለየት ካለበት ሰዎች ሲለይ በጥላቻ መንፈስና አስተሳሰብ ሳይሆን ለማንኛውም ሰው ያለው ርኅራኄ የተሞላበት አስተሳሰብ ለራቃቸውም ሰዎችም እያለውና ለእነርሱም መመለስና መልካምን ነገር እየተመኘ ሊሆን ይገባዋል። ይህም የራቃቸው ሰዎች ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ እነርሱን ይቅር የሚልበትና የሚቀበልበት ልብ እንዲኖረው ያደርጋል።

ሰ. ክርክር

ክርክር በሌሎች ሰዎች ጉዳይ ጣልቃ በመግባት እኔ ያልኩትን የግድ ካልተቀበላችሁኝ ብሎ የእራስን ሀሳብ በፍቅርና በመግባባት ሳይሆን አግባብነት በሌለው እና በእኔነት ተሞልቶ በሌላ ውስጥ ለማስገባት መሞከር ነው። ምሳ 17:14፣ 20:3፣ 25:8፣ 26:17 2 ጢሞ 2:14፣ 24 በማያገባው ጉዳይ ሳይጋበዝ እየገባ በሰው ጉዳይ እኔ ካልዳኘሁኝ፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ፣ እኔ ካልወሰንኩኝ፣ እኔ ያልኩት ብቻ ካልሆነ ማለት ሥጋዊነት ከዚያም በላይ የሚመለከተንና የማይመለከተን ጉዳይ ምን እንደሆነ አለማወቅ እና በሰዎች ሕይወት ለመሰልጠን መጎምጀትም ነው።

ሸ. ቅንዓት

በዚህ ስፍራ የምናየው የእግዚአብሔር ቅንዓት፣ መንፈሳዊ ቅንዓት ሳይሆን የሥጋ ቅንዓትን ነው። ይህ ቅንዓት ለእራስ የሚፈልጉትን ነገር ሌላ ሰው ይዞት ሲያዩ ሰውየውን በክፉ መመልከት ነው። ቅንዖት መራራ የሆነ ውጤትን በማስከተል የሚፈልጉት ነገር የያዘውን ሰው ከስም ማጥፋት ለመጉዳትና ለመግደል እስከማነሳሳት ሊያደርስ ይችላል። ምሳ 14:30፣ 23:27፣ 6:34-35

ቀ. ቁጣ

የሥጋ ቁጣ በጊዜው ማስተዋልን የሚያሳጣ፣ ነገሮች እኔ ባልኩት ወይም ባሰብኩት መስመር ለምን አልፈተጸሙም ወይም የእኔ ነገር ለምን ተነካ፣ በእኔ ላይ ለምን እንዲህ ታሰበ ወይም ተነገረ የሚል የስሜት መነሳሳት ሲሆን በተግባር ከተገለጸ ከፍተኛ አፍራሽ የሆነ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። ምሳ 14:17፣ 19:11፣ መክ 7:9፣ ማቴ 5:22፣ ያዕ 1:19 ክፉውን ለማስወገድ በክፉ ሥራ ላይ እንደ ጌታ መቆጣት ግን መንፈሳዊ ቁጣ ነው።

በ. አድመኛነት

አድመኛነት ለአንድ ክፉ አላማ መጣመርና አንድ ሆኖ በአንድ ወገን ላይ መነሳት ነው። ያዕ 3:14-16 ይህም ለእግዚአብሔር ዓላማ እንደ ቃሉ ቅዱሳን ሊጠብቁት ከሚገባ የመንፈስ አንድነት ተቃራኒ ነው።

ተ. መለያየት

መለያየት የመንፈስ አንድነትንና ጎብረትን ማፍረስ፣ ከእግዚአብሔር ሃሳብ ውጪ ከሰዎች፣ ከቤተሰብ፣ ከቤተ ክርስቲያን፣ ከሕዝብ ወ.ዘ.ተ እራስን መለየትም ሆነ ሌሎች እንዲለዩ ተጽእኖም ማድረግ ሊሆን ይችላል። መለያየትን የሚወድ ምኞቱን ይከተላል። ምሳ 18:1፣ 16:28፣ 29:22። እንደ እግዚአብሔር ሃሳብ መለየት ግን መቀደስ ነው።

ቸ. መናፍቅነት

መናፍቅነት መሠረታዊ የሆኑና የማያሻሙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶችን የሚቃወሙ ትምህርቶችን መስበክ፣ መቀበል፣ ማሠራጨት ነው። ኤር

23:16፣ ማቴ 16:22፣ ቆላ 2:8፣ ዕብ 13:9። መናፍቅ መሠረታዊ የሆኑትንና የማያከራክሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች የማይቀበልና የሚቃወምን ትምህርቶች የሚቀበል፣ በተለያዩ መንገዶች የሚያሠራጭ፣ ወ.ዘ.ተ ነው።

የመናፍቃንን ትምህርት የመቃወም አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም፣ ሆኖም ግን ይህንንም ያንንም መናፍቅ ነው እያሉ በድፍኑ የሚቃወሙ ሁሉ እውነተኞች ናቸው ማለት አይደለም። የአንድ ሰው እውነተኛነት የሚረጋገጠው ሌሎችን በመቃወሙ ሳይሆን እርሱ እራሱ የሚያስተምረው መሠረታዊ ትምህርት ተመዝኖ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። እዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፈው እውነተኛ ክርስቲያኖችን እራሳቸውን የሚያከራክሩ መሠረታዊ ያልሆኑ በማያሻማ መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ባልሰፈሩ አስተሳሰቦች አቅጣጫ ከእኛ የተለየ አስተሳሰብ ያላቸውን እንዲሁም እኛ ያልገባንና ያልደረስንበትን ከመሠረታዊ ትምህርቶችጋር የማይጣረሱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች የሚያስተምሩትን የእግዚአብሔር ሰዎች መናፍቅ ብሎ መፈረጅ መንፈሳዊ ሕፃንነት ከዚያ ካለፈም እራሱ መናፍቅነት ነው።

እንዲያውም አንዳንድ በወንጌል የሚያምኑ ክርስቲያኖች ከእነርሱ አብያተ ክርስቲያን ውጪ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት አባል የሆኑ አገልጋዮች በሙሉ መናፍቃን ይመስሏቸዋል፣ በተለይ አብያተ ክርስቲያኑ በቅርቡ የተመሠረተ ወይም "አዲስ" ከሆነ! እነዚህ እነርሱ ያሉበት "አሮጌ" አብያተ ክርስቲያን ከተወሰኑ ዓመታት ምናልባትም 25 እና 50 ገፋ ቢል ከ75 እና 100 ዓመታት በፊት "አዲስ" የነበሩ እና እግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናትን የመትከል ራዕይ በሰጣቸው ሰዎች የተመሠረተ መሆኑን የተሰወረባቸው ናቸው። በተጨማሪም ከኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይልቅ አባል የሆኑበት ቤተ ክርስቲያን ስም በአእምሮአቸው ጉልቶ የተፃፈባቸውና ሰውን በክርስቶስ ሳይሆን አባል በሆኑበት የቤተ ክርስቲያን ስም የሚያውቁ ናቸው።

በሚቀጥሉት አመታት ዮጵያ ሁሉም ባይሆኑም ብዙዎች ፈተኞች በክርስቶስ ወንጌል በኢትዮጵያ ተፅዕኖ በማምጣት ፈተኞች የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ጎለኞች እንዲሁም በጎላ ከመጡት ከተመሰረቱት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉም ባይሆኑም ጥቂቶች ፈተኞች እየሆኑ ይመጣሉ። የሆኖ ሆኖ ግን የእግዚአብሔር ሀሳብ ፈተኞቹ ከጎለኞች፣ ጎለኞች ከፈተኞች ጋር በጭራሽ እንዲወዳደሩ ብሎም አንዱ ሌላውን እንደ ጠላት በመቁጠር እንዲዋጉ ሳይሆን እርስ በእርስ እንዲረዳዱ፣ እንዲበረታቱ፣ አንዱ መሥራት ያልቻለውን ሥራና ማምጣት ያልቻለውን ተፅዕኖ ሌላው በመሥራትና በማምጣት የአንዱ ጉድለት በሌላው ብርታት እንዲሸፈን ነው። አንዱ በሁሉም፣ ሁሉም በአንዱ እንዲታገዝና የእግዚአብሔር መንግሥት በኢትዮጵያ ብሎም በአለም እንዲስፋፋ ሁሉም የተጠራበት ፍፃሜ ላይም እንዲደርስ ነው። መንፈሳዊ "አባቶች" ሁሉ የአንዱ አባት የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን በመረዳት ለአንዱ መንግሥት ሥራ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳቸው በሰጣቸው ጥሪና አቅጣጫ እጅ ሲሰጣጡና እጅ ለእጅ ተያይዘው ሲሠሩ ይገባል። ገላ 2:9

አንድ አብያተ ክርስቲያን ከጌታ መሆኑና አለመሆኑ የሚመዘነው የአብያተ ክርስቲያኑ ራዕይ ከእግዚአብሔር በመምጣቱና በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት በመረጋገጡ በውስጡ ያሉም አገልጋዮች የሚያስተምሩት መሠረታዊ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ በመሆኑ እንጂ አብያተ ክርስቲያኑ "አዲስ" ወይ "አሮጌ" በመሆኑ አይደለም። እግዚአብሔር የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ራዕይ ብቻ ሳይሆን የአብያተ ክርስቲያን ምሥረታ ራዕይ መስጠት ባለማቆሙ በኢትዮጵያም ይሁን በሌሎች አገሮች ሁልጊዜ መሪያቸውና ጌታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ የሆኑ "አዳዲስ" አብያተ ክርስቲያናት መመሥረታቸውን ሰይጣንም ይሁን ሰዎች ሊያስቆሙ የማይችሉትና የማይቀር ነገር ነው።

ባሉበትም ይሁን በሌላ አካባቢ "አዳዲስ" አብያተ ክርስቲያናት በተመሠረቱ ቁጥር "አዲስ" በመሆናቸው ብቻ የሚደነግጡና የሚብረከረኩ ሌሎች

እንዲብረከረኩ ምክንያት የሚሆኑ መሪዎች በሕይወታቸው ጌታ ሊሠራ ያለውን የማያውቁ ወይም ከጌታ ራዕይ ያልተቀበሉ አለበለዚያም ቀናተኞና ምቀኛ ናቸው። እየተመሠረተ ያለው አብያተ ክርስቲያን ከጌታ ከሆነ ለምስጋናና ጌታን ለመባረክ ምክንያት አይሆንም ይሆንን? የእግዚአብሔር ሀሳብ በወንጌል ዓለምን መድረስና የዳኑትን ክርስቶስ ኢየሱስን ወደ መምሰል የሚያሳድጉ፣ የሚጠብቁና ለአገልግሎት የሚያሰማሩ አብያተ ክርስቲያናትን ራዕዩንና ጸጋውን በሰጣቸው አገልጋዮች መትከል ሲሆን በየትኛውም እውነተኛ አብያተ ክርስቲያናት ያሉ ቅዱሳን ሁሉ በክርስቶስ ሊተዋወቁ የስም አንድነት ሳይሆን ክርስቶስ ኢየሱስን በማወቅ ወደሚገኝ በእውነትና በጽድቅ ላይ የተመሠረተው የመንፈስ አንድነት ላይ እንዲደርሱና ለእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ እስከ ክርስቶስ ምፅአት በተሰጣቸው ጸጋ እርስ በርስ እንዲደጋገፉ ነው።

እዚህ ላይ ጥብቅ ማሳሰቢያ ልንሰጥበት የሚገባ ነገር አለ። ቅዱሳን መናፍቃንን ሲለዩ ከመንፈሳዊ ህፃንነት የተነሳ ገና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ብዙ ስልጠና ሊሰጣቸው የተገቡ ሲሰብኩና ሲያስተምሩ ትምህርታቸውና ስብከታቸው መስመር የለቀቀውን ሁሉ መናፍቅ እያሉ እርስ በእርሳቸው በመጋጨት እርስ በርስ እንዳይጠፋፉ ሊጠነቁ ይገባል። በኦርግጥ በዕብ 6:1-3 ላይ ያሉትን መሠረታዊ የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ያልተማሩ ቅዱሳን በመሰበክና በማስተማር አገልግሎት ከጌታ ከሆነ በተለየ ተአምራታዊ ምክንያት ካልሆነ በቀር መሠማራትም የለባቸውም። አዲ ፣ማኞች ብቻ ባሉበትና አገልጋዮች በሌሉበት ቦታ አማኞቹ የተቻላቸውን ያህል የጌታን ቃል ለመማማር ጥረት ማድረጋቸው የሚደገፍ መሆኑ የሚታወቅ ይመስለኛል።

ነ. ምቀኝነት

ለአንድ ሰው፣ ቤተሰብ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ሕዝብ፣ ወ.ዘ.ተ መልካም ነገር

እንዳይሆንለት መሞከር፣ ነር፣ መታገል ምቀኝነት ነው። ዘፍ 37:4፣ 1 ሳሙ 18:8፣ ማቴ 20:12

ኘ. መግደል

የሰዎችን ሕይወት በተለያየ መንገድ አስቦና አቅዶ ከእግዚአብሔር ሃሳብ ውጪ በሥጋ ክፉ ሃሳብ በመነሳሳት ማጥፋት መግደል ነው። ዘጸ 5:17፣ ማቴ 5:21

አ. ስካር

ስካር አልኮልነት ያላቸውን መጠጦች ከእግዚአብሔር ዓላማ ለምሳሌ፣ ለመድኃኒትነት፣ ወ.ዘ.ተ ውጪ መጠጣት ሲሆን የስካሩ መጠን ሊለያይ ይችላል፣ ከሞቅታ እራስን ሙሉ በሙሉ እስከ መሳት። ምሳ 20:1፣ 23:20. 29-31፣ መክ 10:17፣ ኢሳ 5:11፣ ዕን 2:15፣ ሉቃ 21:34፣ ኤፌ 5:18

ከ. ዘፋኝነት

ዘፋኝነት ለክፉ ድርጊት ወይም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ለሆኑ ነገሮች በአጭሩ ለሥጋ ሥራ የሚያነሳሱ ዘፈኖችን በሙዚቃ መዝፈን፣ ማንጎራጎር፣ ማቀንቀን፣ ወ.ዘ.ተ ነው። ሮሜ 13:13፣ 1 ጴጥ 4:3 ዘማሪነት ለመንፈስ ሥራ የሚያነሳሱ ወደ እግዚአብሔር ፈቃድና ክብር የሚያስገቡ መዝሙሮችን በሙዚቃ መጫወት ነው። የዘፈንና የመዝሙር ዋናው ልዩነት የመልእክትና የመንፈስ እንጂ የሙዚቃና የሙዚቃ መሣሪያ አይደለም። የሙዚቃው ዓላማ የዘፈኑን ወይም የመዝሙሩን መልእክት ማጉላትና ጥም ቆራጭ ውኃ ወደ ሆድ እንደሚገባ መዝሙሩን ልብ ውስጥ ማስገባት ነው።

2. የሥጋ ሥራን ማስወገድ

ከመንፈሳዊ ዕውርነትና ድንቁርና ወይም መንፈሳዊ መሃይምነት ቀጥሎ ሰይጣን ክርስቲያኖችን ለማጥቃት የሚጠቀምበት ከባዱ መሣሪያው በክርስቲያኖች ሕይወት ያለና ያልተወገደ የሥጋ ሥራ ነው።

ከላይ ያየናቸውንና የመሳሰሉትን የሥጋ ሥራን አንድ ክርስቲያን ለማስወገድ፦

ሀ. ለኃጢአት እንደ ሞተ፣ ከኢየሱስ ጋር እንደ ተሰቀለና እንደሞተ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆኖ ለእግዚአብሔር ሕያው እንደሆነ፣ ከክርስቶስ ጋር በመነሣት በአብ ቀኝ በተቀመጠው በክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወቱ እንደ ተሰወረች እራሱን በእምነት መቁጠር አለበት። የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰው ከክርስቶስ ጋር እንደ ተሰቀለና ኃጢአት በእርሱ ላይ ኃይልና ስልጣን የሌለውና ኃጢአትን መቃወም እንደሚችል ተረድቶ ኃጢአትን ለመቃወም የተዘጋጀ ሊሆን ይገባዋል። ሮሜ 6፡5-11፣ ገላ 2፡20፣ 5፡24

ለ. የውሸት አባት የሆነውን የሰይጣንን ሽንገላ ለመቃወም የሚያስችል የእግዚአብሔርን ጦር ዕቃ መልበስና ማንሣት። ዮሐ 8፡44፣ ኤፌ 6፡11፣13

ሐ. የመንፈስን ድምፅ ለመስማት እና የጊዜ ቃል ከጌታ ለመቀበል ያልተቋረጠ ጎብረት ከጌታ ጋር ማድረግ፤ ይህን የሚያደርግ በብርሃን ይመላለሳልና። 1 ዮሐ 1፡6-7

መ. የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነውን ነገር ምን እንደሆነ ፈትኖ ለማወቅ በአእምሮ መታደስ እና ይህን ዓለም አለመምሰል። ይህ ይሆንም ዘንድ ነፍሱን ማዳን የሚችለውን በውስጡ በልቡ

የተተከለውን የጌታን ቃል በየዋህነት መቀበል። ሮሜ 12፡2፣ ያዕ 1፡21

ሠ. አንድ ጊዜ ከክርስቶስ ጋር እንደሞተ በእምነት መቁጠር አንድ ነገር ሲሆን ዕለት ዕለት ደረጃ በደረጃ ለኃጢአት መሞቱ መገለጥ ደግሞ ሌላ ነገር ነው፤ ይኸውም እራሱን እያሳተ ቃሉን የሚሰማ ብቻ ሳይሆን ቃሉን በማድረግ ነው። ቃሉን ሰምቶ የሚያደርገው በሥራው የተባረከ ይሆናል። ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እርስ በእርሳቸው ይቃወማሉ። የሥጋ ምኞትንም ከቶ ባለመፈጸም የሥጋን ሃሳብ በመቃወም አሮጌውን ሰው በማስወገድ የእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድን የሚፈጽም እና የመንፈስ ቅዱስ ምሪትን የሚከተል በመንፈስ ይመላለሳል። ያዕ 1፡22-25፣ ገላ 5፡16-18

ለአንድ ክርስቲያን በእምነት የተቀበለውን በተግባር ለማሳየት፣ የሥጋ ሥራን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ወይም የመንፈስ ፍሬን በሙላት ማሳየት በአንድ ቀን ወይም በአንድ ዓመት የሚወጣው ባለመሆኑ ክርስቲያኖች ሁሉ በትዕግስት እርስ በእርስ ሊተጋገዙና ሊረዳዱ፣ አንዱ ሌላውን በተሰጠው ጸጋ ሊመግብ የሚገባ ሲሆን በኤን አይ ቪ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሜንተሪ (NIV Bible Commentary) እንደ ተጠቀሰው አንድ ክርስቲያንን ከማስተማር፣ ከመምከር፣ ከመገሰጽ፣ በልዩ ልዩ መንገዶች ከመቅጣት፣ ውጪ በሕዝብ ፊት ለማውገዝ ያሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶች የሚከተሉት ብቻ ናቸው።

ሀ. የኢየሱስን ጌትነት እና ኢየሱስ ሰዎችን ለማዳን በሥጋ እንደ መጣ በግልጽ ሲክድ 1 ቆሮ 12፡3፣ 1 ዮሐ 4፡3፣ 2 ዮሐ 7፡10

ለ. ሕዝብ በሚያውቀው የተገለጠ ኃጢአት፣ የሥጋ ሥራ እየተመላለሰ መሆኑን በማያሻማና በማይዋሽበት መንገድ ተደርሶበት ሲገሰጽ በኃጢአት መመላለስን በመምረጥ መንገዱን በንስሐ ለማስተካከል እና የእግዚአብሔር ሰዎችን ዕርዳታ ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር። 1 ቆሮ 5፡1-2፣ 11፣

ከዚህ በስተቀር በሌሎች ምክንያቶች ጉድለት ያለባቸውን ክርስቲያን ወንድሞች በትዕግሥት ጊዜ በመስጠት ማስተማር፣ መገሰጽ፣ ማቅናትና መምከር ተገቢ ነው። ለትምህርት፣ ለተግሣጽ፣ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር የሚጠቅሙ የጌታ መንፈስ ያለባቸው ቅዱሳን መጻሕፍት ተሰጥተውናልና። 1 ጢሞ 3:17 ሆኖም ግን ሰበብ እየፈለጉ ያለ በቂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያት ቅዱሳንን በተለይ አገልጋዮችንና መሪዎችን ማግለልና በሕዝብ መካከል ማውገዝ የመንፈስ ሥራ ሳይሆን የሥጋ ሥራ ነው። በተለይ ለእንደዚህ አይነት የሥጋ ሥራ የተጋለጡ መሪዎች በትክክልም የጌታ ሰው ከሆኑ መሪ ስለሆኑ ብቻ ሁልጊዜ በመንፈስ የሚመላለሱ እና ምንም የሥጋ ሥራ እንደማይሰሩ አድርገው የሚያስመስሉ ወይም ተንኮለኛ ናቸው። አንድ አማኝ በመንፈስ የሚመላለሰው መሪ ስለሆነ ሳይሆን መንፈሳዊ ቤት ሆኖ በመሠራት መንፈሳዊ ሰው ስለሆነ ነው። መንፈሳዊ ሰውም መንፈሳዊ የተሰኘው ሙሉ ሰው በመሆኑ እንጂ በምንም ሁኔታ የሥጋ ሥራ የማይሠራ ሰው ስለሆነ እንዳልሆነ የሚረዳና ሁልጊዜ አራሱን እየፈተሸ ማስተካከል ያለበትን የሚያስተካክል ነው።

መሪዎች በሥጋ ሲንቀሳቀሱ የጌታ መንፈስም ይህንኑ ሊያመለክታቸው ጥፋታቸውን ሸፋፍኖ ለማለፍ የሚያደርጉት ሙከራ ሌላ የባሰ ጥፋት ስለሚያስከትል፣ በቅንነት በንስሐና በይቅርታ የሥጋ ሥራን በማስወገድ ለሌላውም ሕዝብ ምሳሌ መሆን እንደሚጠበቅባቸው መዘንጋት የለበትም። የጌታ ሕዝብ የሚያከብረው መሪ በሕዝብ ፊት የተገለጠውን ጥፋቱን እንኳ ሸፋፍኖ ምንም እንዳልሆነ ለማሳየት በመጣር ዘመኑን የሚጨርሰውን ሳይሆን በንስሐና በይቅርታ አራሱን አያስተካከለ ለሌሎች በንስሐና በይቅርታ መንፈስ መመላለስ ምሳሌ የሚሆነውንና የጌታ ክብር የሚገለጥበትን ሊሆን ይገባል።

- ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፣ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።

- ባለስልጣን የሆኑ ሰዎች የስልጣናቸውን ወሰን ሊረዱና ከተሰጣቸው ስልጣን ውጪ እንደ ናቡከደናፆር በሰዎች ላይ ወሰን የሌለው ስልጣን ለመጠቀም በመሞከር በእግዚአብሔር ቦታ እራሳቸውን በማስቀመጥ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳይጋጩ ሊጠነቀቁ ይገባል።

- አማኝ በክፉ መንገድ ከሚሄዱ ሰዎች እንዲርቅ በጌታ ቃል ተመክሯል። መራቅ ካለበትና መለየት ካለበት ሰዎች ሲለይ ግን በጥላቻ መንፈስና አስተሳሰብ ሳይሆን ለማንኛውም ሰው ያለው ርኅራኄ የተሞላበት አስተሳሰብ ለራቃቸው ሰዎችም እያለው ሊሆን ይገባዋል። ይህም የራቃቸው ሰዎች ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ እነርሱን ይቅር የሚልበትና የሚቀበልበት ልብ እንዲኖረው ያደርጋል።

- ቅንያት መራራ የሆነ ውጤትን በማስከተል የተመቀኙትን ሰው ክስም ማጥፋት ለመጉዳትና ለመግደል እስከማነሳሳት ሊያደርስ ይችላል።

- መንፈሳዊ "አባቶች" ሁሉ የአንዱና የሁሉ አባት የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን በመረዳት ለአንዱ መንግሥት ሥራ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳቸው በሰጣቸው ጥሪና አቅጣጫ እጅ ሊሰጣጡና እጅ ለእጅ ተያይዘው ሊሠሩ ይገባል። ገላ 2:9

- የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያከብረው መሪ በሕዝብ ፊት የተገለጠውን ጥፋቱን እንኳ ሸፋፍኖ ምንም እንዳልሆነ ለማሳየት በመጣር ዘመኑን የሚጨርሰውን ሳይሆን በንስሐና በይቅርታ አራሱን እያስተካከለ ለሌሎች በንስሐና በይቅርታ መንፈስ መመላለስ ምሳሌ የሚሆነውንና የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበትን ሊሆን ይገባል።

ምዕራፍ ስምንት

ፍሬ ማፍራት

ዮሐ 15፡1-5ን ስናነብ ክርስቲያን ፍሬ እንዴት እንደሚያፈራ መንገዱ በግልጥ ተቀምጦ እናገኛለን። ፍሬ የመንፈሳዊ ሥራ ፍሬያማነትን ብቻ ሳይሆን የመንፈስ ፍሬ በማፍራት አቅጣጫ በመውሰድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት ማግኘት እንችላለን። ጌታ ኢየሱስ በዮሐ 15፡4 ላይ ቁልፍ የሆነ ቃል ተናግሯል። ይኸውም፡-

"በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፣ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም።"

በዮሐ 15፡1 ጌታ ኢየሱስ "እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ" ስላለ ቅርንጫፍ የሆነው ክርስቲያን በወይኑ ግንድ ባይኖር በራሱ ፍሬ ሊያፈራ አይቻለውም። ቅርንጫፍ ፍሬ ለማፍራት የሚያስችለውን ምግብ የሚያገኘው ከግንዱ ነው። ስለሆነም በግንዱ ላይ ያልተጣበቀ ቅርንጫፍ ፍሬ ለማፍራት የሚያስፈልገውን ምግብ አያገኝም።

ስለሆነም ክርስቲያን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነት ኅብረት ማድረጉ በሕይወቱ ፍሬ ለማፍራት የሚያስችለውን ያልተቋረጠ ምግብ ለማግኘት ያስችለዋል። ይህ ምግብ በክርስቲያን ሕይወት የመንፈስ ፍሬ ብቻ ሳይሆን ሌሎች የአገልግሎት ፍሬን ለማፍራት ወሳኝ ነው። የአንድ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና የእግዚአብሔር ቃል ሙላት ሳይሆን ከጌታ ጋር የማያቋርጥ ኅብረት ከማድረግ የተነሳ የማያቋርጥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እና

የእግዚአብሔር ቃል ሙላትን መቀበል ወይም የሁልጊዜ መንፈሳዊ ምግብና መጠጥ የመንፈስ ፍሬን በሁሉም አቅጣጫ ለማፍራት እጅግ አስፈላጊ ነው። በእኔ ኑሩ ሲል ጌታ ኢየሱስ ምን ማለቱ ነው? ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ሊኖር ይገባዋል ሲልስ? በክርስቶስ መኖር ማለት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የማያቋርጥ ኅብረት ማድረግ ማለት ነው። ኅብረት ደግሞ አብሮ መጓዝ፣ መስማትና መናገር፣ መውደድና መወደድ ነው። ከዚህም የተነሳ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ኅብረት ማድረግ የእግዚአብሔር ቃልን መስማት፣ ወደ እግዚአብሔር መፀለይ፣ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ መስማት፣ የጌታ ኢየሱስን ፍቅር መቀበልና ምላሽ መስጠት፣ ከእርሱም ጋር አብሮ በሚያድግ ግንኙነት መጓዝን ይጠይቃል። ከጌታ ኢየሱስ ጋር ኅብረት ማድረግ ለመንፈሳዊ ሥራችንም ሆነ በሕይወታችን የመንፈስ ፍሬ በሙላት እንዲታይ እጅግ አስፈላጊ ነው። መዝ 1፡1-3

ከጌታ ኢየሱስ ጋር ኅብረት የሚያደርግ ክርስቲያን፡-

ሀ. የጌታውን ባህሪይ በጥልቀት እየተረዳ ይመጣል። ወደ ላይ ከአብና ከወልድ ጋር ወደ ጎን ከቅዱሳን ጋር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ኅብረት ያደርጋል።

ለ. ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠጋ ቁጥር የጌታው ማንነት እየበራለት ስለሚመጣ ጌታውን እያወቀው ይመጣል።

ሐ. ከመንፈስ ቅዱስ በውስጡ መገኘት የተነሣም የእግዚአብሔር ባህርያት በሕይወቱ እየተቀረፀ ይሄዳል። ሆኖም ግን ይህ ጊዜን የሚጠይቅ እና በአንድ ቀን የማይሆን ነው።

እግዚአብሔር ብርሃን ነው፣ በእርሱ ዘንድ ጨለማ የለም። 1 ዮሐ 1፡5 ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እያደረግህ በጨለማ ልትመላለስ አትችልም። 1

ዮሐ 1:6 በጨለማ መመላለስ ማለት ወንድምን በመጥላት ወይም በሥጋ ሥራ መመላለስ ማለት ነው። 1 ዮሐ 2:9፣11 ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ኅብረት እንዳይቋረጥ ሁልጊዜ በፍቅር ልትመላለስ ይገባሃል። እግዚአብሔር ፍቅር ነውና። 1 ዮሐ 1:7፣ 2:10፣ 4:16 በፍቅር የሚመላለስ እራሱን በቅድስናና ጽድቅን በማድረግ ሲመላለስ ያገኘዋል። በጨለማ የሚመላለስ በርኩሰትና በዓመፀኝነት ለመመላለስ ተላልፎ የተሰጠ ነው።

በገላ 5:22-23 የተጠቀሰው የመንፈስ ፍሬ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያን ሕይወት ከመገኘቱና ክርስቲያን ለመንፈስ ቅዱስ ከመገዛቱ የተነሳ የሚመጣ ውጤት ነው። እነዚህን አስተውል፦

ሀ. መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ይገኛል። ሮሜ 8:9

ለ. ሰው መንፈስ፣ ነፍስና ሥጋ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በእውነት የጌታ ኢየሱስን የአዳኝነት ሥራ የተቀበለ ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስና በእግዚአብሔር ቃል መንፈሱ ዳግም ይወለዳል፣ ነፍሱ እየዳነ ሲሄድ በአሁኑ ዓለም በሥጋው ላይ ካለ ደዌ ፈውስን ሊቀበል ይችላል። ሕያው የሆነው መንፈሱም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ይመሰክርለታል። ሮሜ 8:16፣ ዮሐ 1:12-13።

ሐ. ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ የክርስቶስ ኢየሱስ ባህሪይ እንደ ዘር በክርስቲያኑ ውስጥ ያለ በመሆኑ ዘሩ አድጐ ሲያፈራ የክርስቶስ ባህሪ በክርስቲያን ሕይወት እየተቀረፀ የመንፈስ ፍሬን ያፈራል። 2 ጴጥ 1:3-4።

መ. የመንፈስ ፍሬ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የመገኘቱ ውጫዊ ውጤት ወይም መገለጫ ነው።

ሠ. የመንፈስ ፍሬ እንጂ የመንፈስ ፍሬዎች እንደማይል ገላ 5:22 ላይ ቆይታ ያደረገ ክርስቲያን መረዳት ይችላል። ይህም በፍሬ ውስጥ ያሉ ባህሪያት ተያይዘው አብረው ሳይነጣጠሉ የሚያድጉና የተያያዙ መሆናቸውን ያመለክታል።

በጠቅላላው አማኝ ክርስቶስን ይበልጥ እየመሰለ ለመምጣት ቢያንስ፣

ሀ. ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ ከሁሉ በፊት ማድረግ፣ 1ጢሞ2:1-2

ለ. እግዚአብሔርን ለመምሰል በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ እየተሞሉ የተሞሉትን ያህልም የተሞሉትን ቃልና መንፈስ በሥራ ላይ ለማዋል እራስን ማሰልጠን፣ 1ጢሞ 4:7

ሐ. እግዚአብሔርን መምሰል ዋጋ የሚያስከፍልበት ጊዜ አለ። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆን፣ 2ጢሞ 3:12

"የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን። አሜን።" 2 ቆሮ 13:11

- ☐ በግንዱ ላይ ያልተጣበቀ ቅርንጫፍ ፍሬ ለማፍራት የሚያስፈልገውን ምግብ አያገኝም።

- ☐ ክርስቲያን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነት ማድረጉ በሕይወቱ ፍሬ ለማፍራት የሚያስችለውን ያልተቋረጠ ምግብ ለማግኘት ያስችለዋል።

- ☐ የአንድ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና የእግዚአብሔር ቃል ሙላት ሳይሆን ከጌታ ጋር የማያቋርጥ ጎብረት ከማድረግ የተነሳ የማያቋርጥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እና የእግዚአብሔር ቃል ሙላትን መቀበል ወይም የሁልጊዜ መንፈሳዊ ምግብና መጠጥ የመንፈስ ፍሬን በሁሉም አቅጣጫ ለማፍራት አስፈላጊ ነው።

- ☐ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ጎብረት ማድረግ የእግዚአብሔር ቃልን መስማት፣ ወደ እግዚአብሔር መፀለይ፣ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ መስማት፣ የጌታ ኢየሱስን ፍቅር መቀበልና ምላሽ መስጠት፣ ከእርሱም ጋር አብሮ በሚያድግ ግንኙነት መጓዝን ይጠይቃል።

- ☐ በገላ 5:22-23 የተጠቀሰው የመንፈስ ፍሬ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያን ሕይወት ከመገኘቱና ክርስቲያን ለመንፈስ ቅዱስ ከመገዛቱ የተነሳ የሚመጣ ውጤት ነው።

- ☐ ክርስቶስን መምሰል በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የመገኘቱ ውጫዊ ውጤት ወይም መገለጫ ነው።

- ☐ ክርስቶስን በመምሰል መገንባት የገንዘብ፣ የክብር፣ የግንኙነቶች፣ የእራስን ሕይወት እንኳ የሚያስከፍልበት ጊዜ አለ። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆን ከአማኝ ይጠበቃል።

ክፍል ሦስት
መንፈሳዊ ፅድቅ

"ስዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ። **ክግዚአብሔርን ለመምሰል** ግን ራስህን አስለምድ።"

1 ጢሞ 4:7